# ግንቦት ሰባትን ደግፌ 8 ዓመት ተጓዝኩ!

ሚያዝያ 13ቀን 2009 ዓ.ም(April 21 2017)

ይህንን ፅሁፍ በጥሞና ተከታተሉት፣ እሥከ ዛሬ በእነ ዶክተር ብርሀኑ ለተዘናጋው አማራ ወገኔ ጠቀሜታ ሥላለው።

# ክፍል 1

ሥለ ግንቦት ሰባት እና ኢሳት ከእነ ማስረጃው በሰፊው ወደፊት እመጣበታለሁ፣ ከአሁን ጀምሮ ቢያንስ አንድ ወር ተኩል ቢበዛ ሁለት ወር ልቤ ሳይሆን ቁመናዬ ከግንቦት ሰባቶች ጋር ይቆያል ምክንያቱም አንዳንድ መሟላት የሚገባቸውን መረጃዎቼን እሥካሟላ ድርስ ማለት ነው። ግንቦት ሰባት ከተቋቋመበት ጊዜ አንሥቶ ገንዘቤንም ጉልበቴንም ሣፈስ ኑሬያለሁ። ይህንንም ሳደርግ አመራሮቹ! አማራውን በሰደቡትና በዘረጠጡት ቁጥር ሆዴ ቢደማም፣ ከዛሬ ነገ የኢትዮጵያ አንድነት ዕውን ሊሆን ይችልና ነገሮች ቦታቸውን ይይዙ ይሆናል የሚል ምኞቴና ደካማ ጎኔ እየታገለኝ ነበር።

ምንም እንኳን ሥለ ዶክተር ብርሀኑ ገና (ወያኔ  አዲስ አበባ ከገባ በኋላ) ከአሜሪካ ወደኢትዮጵያ እንደገባ ጀምሮ የማውቃቸው ነገሮች ቢኖሩም፣ በሁለገብ ትግል (በሰላምና በአመፅ) እታገላለሁ ብሎ ግንቦት ሰባትን ይዞ ሲነሳ፣ የሰላሙን ባላምንበትም የአመፁን ትግል ሥላመንኩበት ይህ ሰው <u>ወንድ ወጣው</u> በሚል  ተከተልኩት።

ያም ሆነ ይህ አሁን እኔ ግንቦት ሰባትን አንቅሬ እንድተፋ ያሥገደዱኝን ምክንያቶች  ሥጠቅስ ብርሀኑ ከኢትዮጵያ ከመውጣቱ በፊት የነበሩትን ለወደፊት በሰፊው ሥለምመጣበት እዚህ ላይ አልጠቅስም፣ የምጠቅሰው ከኢትዮጵያ ወደውጭ ከአደረገው ጉዞ በመጀመር ነው።

**1ኛ)** ዶክተር ብርሀኑ  ከእሥር እንደወጣና ወደውጭ ሲጓዝ በመጀመሪያ የሄደው ከኦነግ ጋር ለመገናኘት ወደአረብ አገር ነበር። <u>አንድ የኦነግ ሠው ብዙ ዓመት አረብ አገር ካታር</u> የኖረና <u>አረብኛ አቀላጥፎ የሚችል</u> (ኦነጎችንም ከግብፅ ጋር ያሥተዋወቀ) ግለሰብ፣  ብርሀኑ ከካታር መንግሥትም ሆነ ከሌሎች  የገንዘብ ዕርዳታ እንዲያገኝ ያመቻቸለታል። የግብፁን ጉዳይ ለኦነጎቹ ለእነ ሌንጮ  ጥሎ ወደነጩ ዓለም ተጓዘ። ይህ ካታር ውሥጥ ይኖር የነበረ የኦነግ ሠው በአሁኑ ወቅት መቀመጫውን ግብፅ ውሥጥ አድርጓል።

**2ኛ)** አሁን ለዶክተር ብርሀኑ ገንዘብ በሽበሽ ነው። የገንዘብ ችግር የለበትም። ሥለሆነም ኢሳትን በማቋቋም አምስተርዳም፣ አሜሪካ፣ ለንደን ወዘተ ጋዜጠኞችን በደመወዝ በመቅጠር የፕሮፓጋንዳውን ሥራ ጀመረ።

**3ኛ)** ቀጥሎም ከአረብ አገር የሚገኘውን ገንዘብ ህብረተሰቡ እንዳያውቅ (ህብረተሰቡ ካወቀ ኢትዮጵያን ለአረብ አሳልፎ እንደመሸጥ ሥለሚሆንና  ዓይንህ  ላፈር  ሥለሚያሠኝ)  ለማድረግ  ያለው  አማራጭ፣ የኢትዮጵያ  ማህበረሰብ  እያዋጣ ደመወዝም የሥራ ማካሄጃውንም እንደሚችል ለማስመሰል፣ ለኢሳትም እንዲሁም በአጠቃላይ <u>ለትግሉ</u> ገንዘብ እንድናዋጣ ፕሮፓጋንዳው በሠፊው ተካሄደ። ማህበረሰቡም ሳይሠሥት አዋጣ። ይህ በየጊዜው የሚዋጣው ገንዘብ  ግን የእነ ብርሀኑንና የኢሳትን ጋዜጠኞች ደመወዝና መመላለሻ ወጭ ሊሸፍን ቀርቶ የኢሳትንም የቴሌቪዥን፣ የራዲዮ፣ የቪዥን ኢትዮጵያን የመሳሰሉትን ማካሄጃ እና አገር ቤት በገንዘብ እየገዙ ወሬ እንዲያቀብሏቸው የሚያደርጓቸውንም  ሰዎች ወጭ ለመሸፈን ያዳግተዋል። ይህንንም ግን የሚያውቅ ወይም ቆም ብሎ የሚመራመር ሥንቱ ነው? የሂሳብ ምርመራ ተደርጎ አያውቅም። ግልፅነት ቢኖርና ቢመረመር ኖሮ ጉድ ይፈላ ነበር።

**4ኛ)** ከዚያም ብርሀኑ ከሚኖርበት ከአሜሪካ ሳይንቀሳቀስ “ጀግናው መሪያችን በርሀ ገባ” የሚል ወሬ ተናፈሰ፣ እኔና እኔን

መሰሎች ዕውነት እንዳልሆነ እያወቅን ታማኝነታችን ይሁን፣ ያፍዝ ያደንግዝ ይሆን ወይም ፍርሀት ዝምታን መረጥን። ቀጥሎም ”ለህዝብ ሲል የተደላደለ ኑሮውን ትቶ መከራን የተቀበለው ለሆድ ሳይሆን ለህሊናው የኖረው የዘመናችን ምርጥ ሰው… ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እናከብርሃለን…. እንወድሃለን።” ማለት ተከተለ። ከዚያም ግፊቱ ሲበዛ ወደ አሥመራ ሄደ። አሥመራ ሄዶም ውሎውና አዳሩ ከእነ ኢሳያስና ኮሎኔል ፍፁም የተምነሸነሸ ኑሮ እንደሆነ ከእነ ታማኝና ከኢሳቶች የተሰወረ አይደለም።

**5ኛ**) ይህ በዚህ እንዳለ በወያኔ መሥሪያ ቤቶች የሚገኙ መኮንኖች፣ ወያኔን ለመጣል፣ የማይናቅ ቁጥር ያለው የህብረተሰብ ክፍል ይዘው የገንዘብ አቅም አላቸው ብለው ያሰቧቸውን ቡድኖች ሲያነጋግሩ እነ ብርሀኑንም ገንዘብ እንዲለግሱ ዱባይ ድረስ ጠርተው ጠየቋቸው። ገንዘብም ሠጡ። እኛም 500 500 ዶላር አዋጡ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ አገር ቤት ሥለምንገባ ተባልን። እነ ብርሀኑም ሌሎች ገንዘብ አላቸው የተባሉ ኢትዮጵያኖች ሲጠየቁ ተጠይቀው አዋጡ እንጅ ከመጀመሪያ እሥከ መጨረሻው የኩዴታው ታሪክ ውስጥ ግንቦት ሰባት አልነበረበትም። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ በ6 ወር ውስጥ እንገባለን ብሎ ራሱ ግንቦት ሰባት ኩዴታውን እንደሚያደርገው አሥመስሎ ማህበረሰቡን ማጃጃል ባልተገባ ነበር። ኩዴታውም የግንቦት ሰባት እንዳልሆነ እየታወቀ እነ ዶክተር ብርሀኑ ውሸት ሲግቱን ዛቻቸውንና ሥድባቸውን በመፍራት ፀጥታን መረጥን።

**6ኛ**) ብርሀኑና መሰሎቹ በኢትዮጵያ አንድነት እየተመፃደቁ፣ አማራውን አግልለው የድርጅታቸውን አመራሮች እንደሰርዱን ከራሱ ከብርሀኑ ጀምሮ በጉራጌዎች፣ በከምባቶችና ከአማራ ወይም ከደቡብ ጋር በተጋቡ አንዳንድ ኦሮሞዎች ማሸቃቸው ሲደንቀኝ፣ ብርሀኑ በአንድ ወቅት “አማራው ካልገዛሁ ባይ ነው” ሲል፣ ኤፍሬም ማዴቦ ደግሞ “የት አባቱ አማራ” ብለው በመቀባበል የተሳለቁት ከአይምሮዬ ሊጠፉ አልቻለም። ያውም በኢትዮጵያ አንድነት ሥም፣ እንዲህ ዓይነቱ ዓይን ያወጣ የዘረኝነትና የጥላቻ ንግግር ከትግሬው አይተናነስም።

እንደሚታወቀው በኮሎነል ደመቀ የተቀጣጠለውን ”የአማራ የማንነትና የህልውና ጥያቄ” ሕዝቡ በራሱ ተነሳሽነት በጎበዝ አለቆች የአማራ ተጋድሎ እየተመራ ደሙን እያፈሰሰና ከትግሬ ወራሪዎችና ፋስሽቶች ጋር ግብ ግብ እንደገጠመ ፀሀይ የሞቀው ዓለም ያወቀው ሀቅ ነው።

የአማራው ተጋድሎ በገበሬ ጦር ታጅቦ “<u>በመኖርና ባለመኖር አጣብቂኝ ውስጥሥ ለወደቅሁ፣ እንደእሥከ ዛሬው የሌለ ጦርና ህግ አለ እያልኩ አላልቅም፣ በራሴ ላይ በመተማመን ብቻ፣ ለማንነቴና ለህልውናዬ እየገደልኩ እሞታለሁ”</u> በማለት ተነሥቶ ከትግሬ ዘረኞች ጋር ግብ ግብ ገጥሞ ሲዋደቅ ባህር ዳር ላይ በአንድ ጊዜ 49 አማሮች በትግሬ ዘረኛ ወራሪዎች ሲገደሉ፣ አንዲት እናት ”ከበርሀ ያላችሁ ድረሱልን ወይም መሳሪያ ሥጡን” ብላ ሥትማፀን ከብርሀኑ ጭምር ያልሰማ የለም።

ግንቦት ሰባት 8 ዓመት ሙሉ በኢሳት ፕሮፓጋንዳ አማካኝነት እንደሚዋጋ እየደሰኮረልን ገንዘብ ሲሰብስብ ቆይቶ ባዶነቱን አሥመሥክሯል።እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል ነውና ግንቦት ሰባት ቢኖር ኖሮ “ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ” እንደተባለው በዚህ ጊዜ ከተፍ ይል ነበር። የብርሀኑና የመሰሎቹ የተለመደው ውሸት ከፋብሪካ እሥከሚመዝ ድረስ የአማራ ተጋድሎ ጊዜ ሥላልሰጠው ተጋልጦት አረፈ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ተግባር ሳይሆን ምላስ ብቻ እንደሆኑ አመንኩ።

ከዚያም አማራው ከእንግዲህ ወዲህ የሌለ ኃይል እንደማይጠብቅ እርሙን አውጥቶ ራሱን በራሱ ነፃ ለማውጣት አምርሮ በሚታገልበት ወቅት ጎንደር የሚካሄደውን የአማራውን የህልውና ጥያቄ ሕዝቡ በራሱ ተነሳሽነት <u>የአማራ ተጋድሎ</u> በሚል እንደሚያካሂደው እየታወቀ፣ ብርሀኑና ቡድኑ አርፎ ከቀመጥ ይልቅ መቼም ውሸትና ፀረ-አማራነት አያልቅበትምና አዲስ የቤት ሥራ ይዞ ብቅ አለ። ይኸውም በቅድሚያ የአማራውን ትግል የብርሀኑ-ግንቦት 7 ለማሰኘት ዕቅድ በማውጣት የአማራውን ተጋድሎ “እባካችሁ የግንቦት ሰባት ነው ብላችሁ ከገባንበት ማጥ አውጡን” በማለት፣ ኢሳት የአማራውን ተጋድሎ የነፃነት ሃይሎች” እያለ ዜናውን እንዲያሥተላልፍ ታዘዘ።

“ውሻ በበላበት ይጮሀል” እንደሚባለው ኢሳትም <u>በመጀመሪያ</u> ያደረገው ነገር ቢኖር፣ ጎንደር ላይ ወሬ ነጋሪ በገንዘብ ገዝቶ የአማራውን የገበሬ ትግል የግንቦት ሰባት እንደሆነ ለማስመሰል፣ ግንቦት ሰባት ሳይኖርና ሳይዋጋ፣ በሌለበት አለ ለማሰኘት የትግል ሽሚያውን እንዲህ ሲል ጀመረ “አሸባሪው ወያኔ እንጅ ግንቦት ሠባት አይደለም” የሚል መፈክር ብቅ አለ። <u>ቀጥሎም</u>

ኢሳት ማከሰኞ በነጮች ህዳር 8 ቀን 2016 ዓ.ም ደግሞ ፀረ-አማራ የሆነው የአገው ተወላጅ ፋሲል የኔዓለም የአርበኞች ግንቦት ሰባት ጎንደር ውስጥ ሳይኖር እንዳለ አድርጎ ጠቀሰ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የአማራውንትግልበኢሳትአማካይነት ለግንቦት ሰባት ለማሥረከብ የአማራን ማንነት ከወያኔ ትግሬዎች ባልተናነሰ መልኩ የሚፈታተኑ ብሎም የሚያጠፉ በተለያዩ ከፍሎች የማራቶን መንገዶች ታቀዱ፣

**እነኝህም፣**

(**1ኛ**) በቅድሚያ ብርሀኑ ወጥቶ ከሕዝቡ መካከል ነን እንዲል ተደረገ፣

(**2ኛ**) ቅማንቶቹ ዓለም አንተ ገብረስላሴ (ፕሮፌሰር) እና አበበ ንጋቱ ከብርሀኑ ጋር ሥለሚሠሩ በጎንደር ህብረት አማካይነት ገንዘብ ሠብስቦ በእርዳታ አሥመስሎ ጎንደር ላይ ዘመድ ፈልጎ በመስጠት በአማራነት ሳይሆን በጎንደሬነት እንዲሰባሰ ጥረቱን ተያያዘው። እንደነሱ ፍላጎት የጎንደር ሕዝብ የአማራ ማንነት ካባውን አውልቆ የጎንደሬነት የጎጥ ካባ ከለበሰ በኋላ ግንቦት ሰባትን እንዲቀላቀል ማድረግ ነው። እነኝህ ሠዎች በቅማንትነታቸውም ጭምር ፀረ-አማራ አቋም ሥላለቸው የአማራውን ማንነት በገንዘብ ሊያጠፋ ቆርጠው ተነሥተዋል። ለዚህም ነው ዋልድባ ውሥጥ ከካህናቱ መካከል ጥቂቶቹ በገንዘብ ተገዝተው ሲወናበዱ የታዩት። በተለይ አበበ ንጋቱ ከወያኔዋ አዜብ መሥፍን ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው አማራውን እረዳለሁ ብሎ ሠርጎገቦችን በማስገባት የአማራውን ታጋዮች ሊያሥፈጅ የተላከ የወያኔ ሠላይ እንደሆነ የአማራ ተጋድሎዎች ያወቁት አይመሥልም።

(**3ኛ**) ብርሀኔ መዋ ደግሞ ከብርሀኑ ጋር በቀስተ-ደመና ድርጅትም ሆነ በግንቦት ሰባት ውስጥ አብሮ ሥለሚሠራ አሁን የአማራው ትግል ሲፋፋም በደመነፍስ ተሯሩጦ የጎጃም ሕብረት ፈጥሮ የአማራን ማንነት አጥፍቶ በጎጃም ጎጠኝነት ሊተካ እየተሯሯጠ ይገኛል። ሕዝቡን ከቻለ በጎጃሜነት ካሰባሰበ በኋላ ለብርሀኑ ለማስረከብ ነው።

(**4ኛ**) ደግሞ የወሎ ማህበር የሚል ፀረ-አማራ ቡድንም ከእነ አበበ ንጋቱና ብርሀነ መዋ ተግባር ባልተለዬ መልኩ ደፋ ቀና ሲል ይሥተዋላል።

(**5ኛ**) የአማራ ድምፅ ራዲዮ እሥከ ተቋቋመበት እሥከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ ኢሳት! የኦሮሞ ተገንጣዮችንም ሆነ የሌሎቹን ተገንጣይና የዘር ድርጅቶች ትግል በተመለከተ ሰፊ መድረክ እየሰጠና የሚገኙትንም ዜናዎች ከሚገባው በላይ ለጥጦ በማቅረብ እያሥተላለፈ፣ የአማራውን ትግል ለግንቦት ሰባት አመቻችቶ ለማሥረከብ በሚመሥል መልኩ፣ የአማራውን ብሶት ሊያሥረዱ የሚችሉ የፖለቲካ ተመክሮና ዕውቀት ያላቸውን አማሮች ሆን ብሎ በረቀቀ መንገድ እያራቀ "እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው" ዓይነት ፀረ-አማራ ተግባሩን እዚህ ላይ አንድ ብሎ ጀመረ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን የውሸት ዜና ማሠራጫዎች ሥለጠላ፣ በወቅቱ ኢሳትን እንደ አማራጭ ወሰደ። ኢሳትም "በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ሥለታወቅሁ የፈለገውን ብናገር እታመናለሁ እና አማራውን በረቀቀ መንገድ ታግዬ ባዳከመውምና ለብርሀኑ ባሥርክበውም ማንም ተራ ሠው አይገባውም" ብሎ ያስባል።

ሕዝብ ሲወድም ይወዳል፣ ሲበደልና ክህደት ሲፈፀምበት ደግሞ አይቶ አይቶ አንቅሮ ይተፋል። ኢሳት እንዲህ ዓይነት የመሠሪዎች መሣሪያ በመሆን አረንቋ ውስጥ ተደፍቆና የዜና ኃላፊነቱን እንደዘነጋ አልተረዳም አይባልም፣ ጠንቅቆ ያውቀዋል፣ ግን ሆን ብሎ ሎሌነቱን ቀጥሎበታል። ምክንያቱ ቅጥረኝነቱ ነው ብንል መሳሳት አይሆንም። ቀኝም ነፈሰ ግራ ሆላንድም፣ እንግሊዝም ሆነ አሜሪካ ወዘተ... የሚገኙት ኢሳቶች ደመወዛቸው የሚሰፈርላቸው ከብርሀኑ እንደሆነና ኢሳትንም ብርሀኑ እንደፈለገ እንደሚያደርገው ማንም አይሥተውም፣ አለዚያማ ከሥራ ይባረራሉ።

ሥለዚህ ኢሳት ውስጥ ያሉ ሠዎች ያመኑበትን ሳይሆን "በሉና ተናገሩ" የተባሉትን ብቻ እንደሚያደርጉ ለሁላችንም ካልተገለፀልን ከዛሬ ጀምሮ ፍንትው ያለ ሀቅ ሥለሆነ ይግባን። የሚያሥተባብል ካለ ደግሞ የሂሳብ ምርመራ ወይም ኦዲት ይደረግና እንዬው። ኦዲትማ ከተደረገ ጉድ ይፈላል።

“ውሻ በበላበት ይጮህል “እንደሚባለው፣ ኢሳት ብርሀኑን ከገባበት የውርደትና የውሸት ረግረግ ለማውጣት የአማራውን ትግል የግንቦት ሰባት እንደሆነ በማሥመሰል በቦታው የሚንቀሳቀሱትና ወያኔን የሚፋለሙት በአማራ ማንነት ዙሪያ የተሰባሰቡ “የአማራ ተጋድሎዎች” እንደሆኑ እያወቀ፣ “የነፃነት ኃይሎች” በሚል ማሥተላለፍ የአማራ ተጋድሎ ላለማለት በአማራው ትግል ላይ ውሀ ሲቸልስ ተሥተውሏል። ኢሳት ለብርሀኑ ጥብቅና በመቆሙ በአማራነት የሚደራጀውን ኃይል በረቀቀ መንገድ ለብርሀኑ ለማሥረከብ ሲጥር ከርሟል። ግን ግንቦት ሰባት ሳይዋጋ፣ የአማራውን ድል በፕሮፓጋንዳ ለመቀማት የሚሯሯጠው ዘለቄታ ይኖረዋል ብሎ ነው ወይስ ሠውን ግራ በማጋባት የኢሳያስ አፈወርቄን ፀረ-አማራ ሥራ እየተገበረ ነው ብዬ ብዙ ጊዜ ራሴን ብጠይቅም መልስ አላገኘሁም።

እሥካሁን ግንቦቶች ያደረጉትን አድርገውም የአማራው ተጋድሎ ጠንክሮ ትግሉን በመቀጠሉ ግንቦት ሰባት የሚይዘውን ሲያጣ ያው የተለመደውን የአማራውን የተጋድሎ ትግል የእኛ ነው ማለቱን ቀጠለ ምክንያቱም “የአማራው ጎበዝ አለቆች በብዙ ቦታዎች ራሳቸውን አደራጅተው ቢንቀሳቀሱም በአንድ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ተሰባስበው ሥለማይገኙ፣ በያሉበት ገንዘብ ይዘን ከቀረብን አንዱ እምቢ ቢል ሌላው እሺ ይለን ይሆናልና እንሞክር” ዓይነት አካሄድ ሥለሚያራመዱ ይመስላል። ግን ውጤት አልባ ሆኗል።

# ክፍል 2

ከዚህ ውጤት አልባ ከሆኑበት ቀን ጀምሮ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ መፈራገጥን መረጡ። ምንም እንኳን ዕውነትን ብርሀኑ ጋ ፈልገን ባናገኛትም እሥኪ ከራሱ ደጋፊዎች ቀረቡለት ለተባሉት ጥያቄዎች የመንታ ምላስ መልስ እንሥማ፣

**ጥያቄ 1!** በአማራ ክልል ራሳቸውን የጎበዝ አለቃ ብለው ካደራጁ ወገኖች ጋ ያላችሁ ግንኙነት ምን ይመስላል? አብራችሁስ እየሠራችሁ ነው ወይ?

**የብርሀኑ ዓይን ያወጣ መልስ!** በዚያ ትግል ውስጥ ግንቦት ሰባት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከጎበዝ አለቆቹ ጋር በመገናኘትና በማደራጀት ሥራ ከሞላ ጎደል እየሠራን ነው፣ ከሞላ ጎደል ልምምድ እየሠጠን ነው። እርዳታም ለመሥጠት እንሞክራለን። ትግሉን እየመራሁ ያለሁት እኔ ነኝ የሚሉ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚነሱ ነገሮች እንዳሉ እንሰማለን። በአሁኑ ወቅት እየተደረጉ ያሉትን ትግሎች የነፃነት ኃይሎች እያለ እንዲነገር አሥደረግነው እንጅ አርበኞች ግንቦት ሰባት ነው እየታገለ ያለው። ይህን ያሥደረግነው “እኛ ነን ትግሉን የምንመራው፣ እሚለው አተካራ ላለመግባት ነው።

**መልስ 1 !** ምን ነካው ብርሀኑ! ዓለም ያወቀውን ፀሀይ የሞቀውን ሀቅ መካድ ጤንነት ይመሥላል? ሳላውቅ 8 ዓመት ተከትዬ ነበር፣ የግንቦት ሰባት የውሸት ክምር ከእንቅልፌ ሥላነቃኝ ከዛሬ ጀምሮ ወያኔን እንደምታገለው እታገላችኋለሁ። “አተካራ” ውስጥ ላለመግባት ብለን ነው፣ ያለን ሰውዬ በሰው ድል ለመክበር ዛሬም ድረስ ከውሸት ላይ ውሸት እየደራረበ በሄደ ቁጥር ከአታካራ ሊወጣ እንደማይችል እንዴት አጣው። “አይታፈርም ወይ?” ድል ሳያደርግ አደረግሁ፣ ሳይተኩስ ተኮስኩ፣ ሳይገድል ገደልኩ እያለ ሀፍረት የሚባል የማያውቅ፣ ኢትዮጵያዊ ባህል ያልተላበሰ በሌላው ኪሳራ አንቱ መባልንና ለሥልጣን መቋመጥን መመሪያው ያደረገ አይቼም ሠምቼም አላውቅም፣ ይሉኝታ የሚባል ነገር አብሮት እንዳልተፈጠረ ሥራው ምሥክር ነው። ምንም ብዘገይም፣ ማንነታችሁን በመረዳቴ ፈጣሪዬን አመሠግነዋለሁ። ግን የምሠጋው አንድ ነገር ቢኖር፣ በብርሀኑ ግንቦት ሰባት ሥም ሌላው የአማራ ጠላት ሻዕቢያ በተዘዋዋሪ በጀርባችን እንዳይወጋን ብቻ ነው እንጅ የብርሀኑስ ነገር ይብቃን።

**ጥያቄ 2!** ትግሉስ ተስፋ አለው ወይ ተብሎ ሲጠየቅ፣

ብርሀኑ የሰጠው መልስ! ባጭሩ ከአንድ አመት በፊት እንዲህ ያለ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በአገሪቱ ውስጥ አይታይም ነበር፣ በአሁኑ ወቅት ይኸ ሁሉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ዛሬ የምታዬው ድርጅታችን ሥራውን ሥለሠራ ነው።

**<u>መልስ 2</u> !** ይህ የብርሀኑ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ንግግር ከራሱ ጋር እያጣላና ልቡን እያሳሳ ምላሱን ያጎለብትለታል እንጅ አንዲት ሚሊሜትር ነፃ መሬት አያጎናፅፈውም።

የአማራውን ትግል በተመለከተ ብርሀኑ ሳይሠራ ሠራሁ ብሎ እንደሚመኘው ሳይሆን የሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት፣ የወልቃይት ኮሚቴና ሌሎቹም የአማራ ተጋድሎዎች እንዲሁም በአጠቃላይ በአማራው ሕዝብ ማንነትና ህልውና ላይ የሚደረገው የግፍ ፅዋ ሞልቶ በመፍሰሱ ነው ትግሉ አሁን እደረሰበት ደረጃ ላይ የደረሰው።

**<u>ጥያቄ 3</u>!** ሥለ ወልቃይት ጉዳይ?

**ብርሀኑ ሥለወልቃይት ተጠይቆ ሲመልስ!** የወልቃይት ጠገዴም ሆነ እንደዚሁም በአፋር አካባቢ የሚነሱ <u>የማንነት ጥያቄዎች ወያኔን በጋራ አሥገድደን ወይም አሥወግደን ከጣልን በኋላ፣ ያን ዲሞክራሲያዊ ሥር ዓት ከፈጠርን በኋላ</u> <u>የጨዋታው ህግ ለሁሉም እኩል ከሆነ በኋላ የምንታገለው ትግል ይሆናል፣ ሕዝብ ራሱ የሚወስነው ይሆናል</u>። <u>ዝምብሎ</u> <u>አቧራ ማሥነሳቱን አቁመን ወያኔን ለመጣል</u> በጋራ እንነሳ።

**<u>መልስ 3 !</u>** ምነው፣ ምነው ብልጡ ብርሀኑ! "ወያኔን በጋራ አሥገድደን ወይም አሥወግደን፣ ያን <u>ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ከፈጠርን በኋላ የጨዋታው ህግ ለሁሉም እኩል ከሆነ በኋላ የምንታገለው ትግል</u> ይሆናል" ብሎን አረፈ። አማራው ትግሬውን ሥልጣን አቆናጦ ሲደማ እንደሚኖረው፣ ብርሀኑና መሰሎቹን ከእነ ሌንጮ ኦነግ ጭምር በተራቸው ሥልጣን ካቆናጠጠ በኋላ የበታችነቱን አውቆ ይኑር ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህ ደግሞ አይታሰብም። <u>በቅድሚያ ማስታውስህ አማራ አሁን የሚታገለው ከምድረ ገፅ እንዳይጠፋ ለህልውናውነው። አንተ ብርሀኑ ደግሞ በዴሞክራሲ ሥም የወያኔና የኦነግን የብሔር አንቀፅ 39ና ክልልን በሌላ መልክ ተግባራዊ ለማድረግ ነው</u>፣ ለዚህም ነው የዘር ድርጅቶችም በአንተ አፈቀላጤነት በእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካዊ ተግባር የተጠመዳችሁት።

አማራን እሥከዛሬ በአንድነትና በኢትዮጵያዊነት ሥም ወዘተ እያዘናጋችሁ ሥታርዱትና ሥትገሉት ኑራችኋል፣ከእንግዲህ ግን "ሞኝን ሁለት ጊዜ እባብ ነደፈው" አይሆንም አታሞኙትም፣አታዘናጉትም።

<u>አቧራ ማሥነሳትን በተመለከተ!</u> ዶክተር ማለት ደንቆሮ ማለት እንዳይሆንብኝ ሠጋሁ። አንተን ነው እንጄ 8 ዓመት የተከተልኩት? ምን ነክቶኝ ነበር? ብርሀኑ! መሙለጭለጬን ትተህ፣ ልብ ብለህ አድምጥ፣ የአማራው የብዙ ዓመታት ብሶት ተጠራቅሞ፣ ከሚሸከመው በላይ ሥለሆነበት በወልቃይት ኮሚቴ አማካይነት የአማራው የህልውና ትግል ሊፈነዳ ችሏል። ወያኔ ይህን የወልቃይት አማራነት ባለመቀበሉና ባለማክበሩ አማራውን እያባረረ ትግሬዎችን እንዳሰፈረበትና ለአማራው መሰደድና ጫካ የመግባት ምክንያት የሆነን ግዙፍ የአማራው ሕዝብ ጥያቄ በማናናቅ <u>"ዝም ብሎ አቧራ ማሥነሳቱን አቁመን ወያኔን ለመጣል"</u> እያሉ ማናፋትና መንታ ምላስ መጎልጎል "በሰው ቁስል እንጨት ሥደድበት" የሆነ የፀረ-አማራነት ተግባር ከመሆን አይዘልም። ባንቀልባ ያዘላችሁት ኢሳያስ አፈወርቂ የኢትዮጵያና የአማራ ጠላት መሆኑንና በእሱም ትዕዛዝ ኤርትራ ላይ ፀረ-አማራ የሆናችሁትን የግንቦት ሰባትን፣ የአፋርን፣ የሲዳማንና የእነ ሌንጮን የዘር ድርጅቶች ሰብስቦ፣ መልከ ጥፉ በሥም ይደግፉ የሆነ "የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ" ተብዬውን ፈጥሯል። የተፈጠረው ኤርትራ ውስጥ ነው፣ እሱም ፀረ-አማራ ነው። አሜሪካ ሥትመጡ ደግሞ አዲስ ድርጅት እንደምታቋቁሙ አሥመሥላችሁ በድጋሜ ያንኑ የዘር ሥብስብ ድርጅት፣ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ የተባለውን ባንዳ አፈቀላጤ አድርጋችሁ ብቅ አላችሁ።

**<u>የግንቦት ሰባት አመራር ነን ባዮቹ የጉራጌና የከምባታ ነፃ አውጭዎች ከአንዳንድ እንከርዳዶች ጋር በመሆን በአማራው ላይ የሚያደርጉት</u> <u>የጥላቻዘመቻ!</u>**

ይህ በዚህ እንዳለ አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ <u>የጉራጌ ጎሳና የከምባታ ጎሳ ግንቦት ሰባት አመራር</u> በተለያዩ አካባቢዎች ያቋቋሟቸውን ሕዝባዊ መገናኛዎችን በመጠቀም፣ በየቦታው ተሰማርተው ከወያኔ ከሻዕቢያና ከኦነግ ባልተናነሰ መልኩ አማራን በምላሳቸው ለመቀጥቀጥ የፀረ-አማራውን ፕሮፓጋንዳ በማጧጧፍ ቃለ ምልልስ በቃለምልልስ በመሆን ተጠምደዋል።

ከእያንዳንዳቸው ንግግሮች የተወሰኑትን በአጭሩ ጠቅሼ ላቁም።

**ሻዕቢያ፣ አነግ፣ ወያኔ!** ሁሉንም አማራ በአንድ ቅርጫት ከተው፣ በሥሙ "አማራ" ብለው እየጠሩ ሊያጠፉት ቢሞክሩ፣ በሁሉም አካባቢ የሚኖረው አማራ በአንድ ሌሊት ተነሥቶ ድምጥማጣቸውን ያጠፋው ነበር። ሥለዚህ ጠላቶች የመረጡት አዋጭ የትግል መንገድ "የዱሮ ሥራዓት ናፋቂ፣ ፊውዳል፣ ትምክህተኛ ወዘተ" እያሉ አንድ በአንድ በዝርዝር መጨፍጨፍን ነው።

ብርሀኑና መሰሎቹ ደግሞ ለእነወያኔ የሠራው ለእኛ ለጉራጌዎቹና ለከምባታዎቹ የማይሠራበት ምክንያት የለም በሚል ይመስላል፣በተራቸው ከወያኔዎች ለዬት ያለ ሥም ሠጥተው አማራውን "አክራሪ" በማለት ወያኔዎችን ከሚያወግዙት በላይ አማራውን በማውገዝ የዘመቱበትን እንከታተል፣

# ብርሀኑ ነጋ !

(1) "ለዛሬ ችግራችን መፍትሄ ሥንፈልግ በኋላ ታሪካችን የፍጥኝ ታሥረን መፍትሄውን ከታሪክ እናገኘዋለን ብለን ታሪክን በመቧጠጥ የምናገኘው ሳይሆን፣ የወደፊቱን ጥሩ መሠረት ላይ ለማቆም ያለመ የዛሬ መፍትሄ እንደሚፈልግ አውቀን ነው። የዛሬይቱ ዓለም ያለችበትን ሁኔታና አገራችን በዚች ዓለም ጠገግ ውስጥ እንጅ በታሪክ ዓለም እንደማንኖር እንረዳ" ባይ ነው።

**መልስ!** "አማራ ደጋግመህታሪክህን ትነግረናለህ፣ በኋላ ታሪክህ የፍጥኝ ታሥረህ መፍትሄውን ከታሪክ አገኘዋለህ ብለህ ታሪክን አትቧጥ፣ በታሪክ ዓለም አትኖርም፣ለወደፊቱ ጥሩ መሠረት ለማቆም የዛሬ መፍትሄ ነው የሚያሻው" ይለናል።

ይህ ማለት ባጭሩ ዛሬ ወያኔም፣ አነግም ግንቦት ሰባትም "የቆየውን ነባሩን ታሪክ ሥለማናምንበት ታሪክ ታሪክ አትበሉ" በሚል እድንሸማቀቅ የሥነ ልቦናና የህሊና ጦርነት ሲያካሂዱ ኖረዋል፣ ዛሬም ለማሥተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ከጥንቱ የተለዬ ባለመሆኑ ለባንዳዎች ጀሮ የለንም።እነእምዬ ምንሊክን እነአፄ ቴዎድሮስን የግንቦት ሰባት ባለሚል እነኦነግና መሰሎቹ ሲያወግዟቸውና የመወንጀያ ሀውልት ሲሰራባቸው፣ አማራው ተነሥቶ ጋሻና መከታ መሆኑ ያልተዋጠለት የውሸት አንድነት ጠበቃ ብርሀኑ ነጋ ምላሱን ዘርግቶና አፉን ሞልቶ ታሪካችንን ለማጣጣል መሞከሩ በአማራው ላይ ያለውን ጭፍን ጥላቻ ለመተግበር እንደሆነ ግልፅ ነው።

(2) "በተወሰኑ ወቅቶች የማህበረሰቡን በተለይም የወጣቱን ቀልብ ለመሳብ የሚችሉ፣ ሥሜታዊ መፈክሮችና የበደል ሥሜቶች፣ በተለይ በአክራሪ ኃይሎች (በአማራዎች) ሲቀነቀኑ፣ ጊዜያዊም ቢሆን ተሰሚነት ሊያገኙ እንደሚችሉና ማህበረሰቡን አደገኛ ቀውስ ውስጥ ሊከቱት ይችላሉ"፣ ካለ በኋላ አክራሪዎች (አማራዎች) ማህበረሰቡን በስሜት ለመጋለ በሚሞክሩበት ጊዜ እነሱ ካላቸው የማጥፋት እልህና ቆራጥነት ባልተናነሰ በቆራጥነት መቆምና መታገል ይገባችኋል። በምንም ዓይነት በሥሜት ለሚጋልቡ የፖለቲካ ኃይሎችና በጣም በመጮሀቸውና የከረረ አቋም በመያዛቸው ከመድረክ እናባራለን ብለው ለሚያምኑ፣ በፍፁም መድረኩን አትልቀቁላቸው።

**መልስ!** የብርሀኑ ጭብጥ መልዕክት የሚነግረን፣ "አክራሪ ኃይሎች (አማራዎች) ሥሜታዊ የበደል መፈክሮች ይዘው ሲነሱ ተሰሚነት ሊያገኙ እንደሚችሉና ማህበረሰቡን አደገኛ ቀውስ ውስጥ ሊከቱት ሥለሚችሉ ከእነሱ የማጥፋት ቆራጥነት ባልተናነሰ መልኩ በቆራጥነት ታገሏቸው፣ መድረኩንም አትልቀቁላቸው"ይላል ለደጋፊዎቹ።

ዛሬ አማራው በመኖርና ባለመኖር መካከል ወድቆ ለህልውናው እየታገለ በሚገኝበት በዚህ ከውጢ ወቅት በአጠቃላይ በአማራው ዘር ላይ ጦር ታውጆበት፣ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደበትና እየተዋደቀ በሚገኝበት ጊዜ በአማራው ተጋድሎ

ላይ ዝሙቱበት የሚል ቅሥቀሳ ማካሄድ የወዳጅ ነው ወይስ የጠላት ሥራ?

አማራው ከምድረገፅ እንዲጠፋ በትግሬ ዘረኞች መንግሥት ተብዬው በአዋጅ ጭምር ተደንግጎበት በሚገኝበት በዚህ ወቅት "የዕብድ ገላጋይ ዱላ ያቀብላል"እንዲሉ ከጎንህ ነን ከማለት ይልቅ"እኛ ሳይሳካልን፣ አማራው ጦር ይዞ ወያኔን እየተፋለመ እኛን አጋልጦናልና አማራውን አክራሪ በሚል ሽፋን በፕሮፓጋንዳ ታገሉት፣ አጥፉት የሚል የተሰፋ መቁረጥ እርኩሳዊ መልዕክት ማሥተጋባት ለኢትዮጵያ ታሥቦ እንዳልሆነ ገሀድ ነው።

በነገራችን ላይ፣ ዛሬ ቁጥራቸው የማይናቅ አማሮች ኤርትራ ገብተው በእነብርሀኑ ተባባሪነት የቁም እሥር እንደሆኑና ቀልጠው እንደቀሩ ሳስብ፣በተቃራኒው ግን ጉራጌዎቹ፣ ኦሮሞዎቹ፣ ከምባቶቹ ወዘተ የኢሳያስ ባለሚል ሆነው ላይ ታች ሲሉ ማዬቴ ገርሞኝ ኑሯል። ኢሳያስን ከእነ ብርሀኑ፣ ከእነአነግ፣ ከእነማዴቦ ከገንጣይ አሥገንጣዮች ጋር ምንድነው ወርቅና ሠም አድርጎ ያሥማማቸው ብዬ ሳስብ እሥከቅርብ ጊዜ አልተገለፀልኝም ነበር። ዛሬ ግን ፍንትው ብሎ ታዬኝ። ይኸውም አሁን የሚያደርጉት ፀረ-አማራና ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነት ብቻ እንደሆነ ተረዳሁ። እነብርሀኑ የኢትዮጵያን አንድነትሥሙን ብቻ ይዘው አማራውን ለመድፈቅ ያቋቋሙት የአንዳንድ  በጋብቻ የተጠመዱ ኦሮሞዎችና የደቡብ ፀረ-አማራ ቡድኖች ክምችት እንደሆነ ተግባራቸው መሥክሯል።

# ክፍል 3

## <u>ነዓምን ዘለቀ!</u>

(1) ሌላው  የግንቦት ሰባት ጉድ ነዓምን ዘለቀ ደግሞ ኢ.አ.አ ከማርች 26 እሥከ ማርች 27 2016ዓ.ም "ቪዥን ኢትዮጵያ" በሚባለው መድረክ ላይ የተቀመጡትን የኦሮሞ ልሂቃን ለማሥደሰት በሚመስል መልኩ የግንቦት ሰባት ተብዬውን ወክሎ ሲናገር፣ ሲቃ እየተናነቀው "እኔ ኢትዮጵያ የምትባል አገርና የኢትዮጵያ አንድነት ብቻ ሲባል ሰፎኬት ያደርገኛል"(ያፍነኛል፣ ያቅለሸልሸኛል) እያለ ሲቧርቅ ታዝበናል። ምንም እንኳን ባንቀበለውም፣ከዚህም ሌላ ብዙ ብዙ ብሏል።ታዲያ በምን መሥፈርት ነው ከወያኔና ከሻዕቢያ እንዲሁም በቅርቡ ለንደን ላይ "ኢትዮጵያ ካልጠፋች ኦረሚያን መገንባት አይቻልም" ካለው ደንቆሮ ኦነግ (ሊበን ዋቆ)የሚለዬው?

ለኦሮሞ አክራሪዎች ቃል የገባላቸው በሚመስል መልኩ ሊነግረን  የፈለገው "እናንተ አማራዎች ፈለጋችሁም አልፈለጋችሁም ከዚህ ቀደም ኤርትራ ሄዳችሁ በድለናል ይቅርታ እንድትሉ እንደተገደዳችሁት ሁሉ፣ከኦሮሞ አክራሪዎች  የሚደረጉትንም ጫናዎች ብትወዱም፣ብጠሉም ትቀበሏታላችሁ" ነው ጥረቱ።

አማራ ማንንም በድሎ አያውቅም፣ አማራ ግን ተበድሏል፣ ተሳዷል፣ ታድኗል። ማንም እየተነሳ በአማራው ላይ የሚጨፍረውና አማራውንም ያሥደፈረው ከሀዲዎች በበዙባት አገር ብቻውን አንድነት አንድነት ማለቱ ነው።"ሥለዚህ አማራውን እንደህፃን ልጅ እየተነሳን የፈለገውን አምጣ ብንለው፣ ሌላው ቀርቶ ብንገለው እንኳን የኢትዮጵያ አንድነትን ሥለሚወዳት የትም አይሄድም። አፈንጋጮቹንና ተገንጣዮቹን ነው ማባበልና ማስደሰት ያለብን" የሚል ግልብ ፖለቲካ የትም አያደርስም። አማራ አሁን መሮት ተነሥቶ የሚታገለው ሥለህልውናውና ሥለማንነቱ ብቻ እንጅ ነዓምን እንደሚመኘው አይደለም። ዛሬ አማራው የሚታገለው ማንነቴን አልሸጥም በማለት ለማንነቱና ለህልውናው የአርበኝነት ትግል ነው። ታዲያ በዚህ ወቅት "ፍዬል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" የሆነ የእናንተ አየር በአየር የቃላት ድርድር፣ ፍትህ፣ ዲሞክራሲና እኩልነት ብሎ ማቅራራ፣ በመኖርና ባለመኖር መካከል ለሚገኘውና ከምድረገፅ እንዲጠፋ በትግሬ ዘረኞች ጦርነት ለታወጀበት አማራ ምን ይፈይዳል?

**ነዓምን!** ለኦሮሞ አክራሪዎች እንዲያጎነብስ የምታደርገውን ሽር ጉድ ነቅተንብሀልና አቁም። በአማራው ላይ እሥከዛሬ የተደረገው የሥነ ልቦና ሠለባ ይብቃ።

የትግሬን ዘረኞች ከመታገል ይልቅ ዛሬም ከአማራው ራስ ላይ ያልወረዱትን የኦሮሞ አክራሪዎችንና ተገንጣዮችን ተግባር ሥኬታማ ለማድረግ ከፊት ለፊት ቀደም ቀደም እያሉ በአማራው ላይ ጫና በማስቀመጥ ሲወዘውዙት ይሥተዋላሉ። ውሸት ሲደጋገም ዕውነት ይሆናል። የብአዴን አባል የነበሩ፣ ሕዝብን ሲያስጨፈጭፉ የነበሩ፣ የወያኔ መሣሪያ አንጋች የነበሩ ይላል ነዓምን።

ነዓምን! እንደምትዋሸው ሳይሆን እነኚህ ሕዝብን ያሥጨፈጨፉ የብአዴን አባላት የምትላቸው ንፁህ ወጣት አማራዎች ከፊሎቹ በተገኘው የሥራ መስክ ከድርጅት ሥራም ጭምር ገብተው ቢሠሩም ነቅተው በፊት ለፊት ወያኔን ተጋፍጠው ከፊሎቹ የጫካውን ሲቀላቀሉ፣ ከፊሎቹ ተሰደው ይታገላሉ። ሕዝብን ያሥጨፈጨፉ የሚለው አባባል ግን የፖለቲካ ትርፍ ያሥገኝልሀ መሥሎህ የምትጠቀምበት የኪሣራ ንግግርህ ነው።

(2) ማንኛችንም በእርግጠኝነትና በድፍረት መናገር የምንችለው ከማህፀኗ ሥለወጣን <u>እናትን</u> በተመለከተ እንጅ <u>አባትን</u> በተመለከተ "አባትህ ነው፣አባትህ ነኝ "ሥንባል ብቻ እንጅ፣ከነዓምን ጀምሮ ማንኛችንም በእርግጠኝነት መናገር አንችልም። እጅግ በጣም የገረመኝ ግን ነዓምን ዘለቀ ከኤርትራ ዘር እንዳለው በቅርብ የምናውቀውን ሀቅ ሸምጦ መካዱና ለምን ቁስሌ ተነካ በሚል "ሞረሽና አማራ የሚሏቸው ሥሜን እያጠፉ" በሚል፣እሱ ራሱ ዋሽቶ ሌላውን በመወንጀል ሀቀኛ ለመሆን ሲጥር ነው።"የአይጥ ምሥክሯ ድንቢጥ" እንዲሉ አቶ በትሩ ይጠየቁ ብሎን አረፈ። አቶ በትሩ እግር ካልያዙ በሥተቀር እንዴት ያውቃሉ?

የነዓምን ዘር ከተነገረ ዓመታት አልፈዋል፣ዛሬ ለምን አዲስ ሆነበት ብዬ ራሴን ሥጠይቅ ያገኘሁት መልስ፣የአማራን ትግል ለመጥለፍ ቢሞክሩም፣ በውጭ እነሞረሽና መሰሎቻቸው፣ በአገር ቤትም የአማራው ተጋድሎ እያየለ ሥለሄደ፣ ቁጣውንና ንጭንጩን በእነሞረሽ ላይ ለመወጣትና 75 በመቶ አማራ ነኝ ማለትን መረጠ። ሞረሽን ለመንካት የተፈለገው፣ የሞረሽ አመራር በሚገባ ግንቦት ሰባትን እርቃኑን ሥላሥቀረው እንደሆነ የታወቀ ነው።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ትልቅ ማዕረግ ደረሱ የተባሉት ብዙዎቹ አርበኞች ሳይሆኑ የኤርትራና የሌላ አካባቢ ባንዶች እንደነበሩ አትሥተውም፣ሥለአባትህም ማዕረግ ብዙ ሥትል ሥለሰማን፣ በኩራት ለመናገር አትድፈር።

ዘረኛው ወያኔ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ማለትም ለ25ዓመት <u>አማራው ከልቡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ አንድነት</u> ሲታገል፣ አማርኛ ቋንቋን እየተናገሩ ከአማራው ጋር የሚታገሉ በመምሰል የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ አንድነትን ከአንገት በላይ እየቀረቡና እየነገዱ ሲያስጨርሱን ኖረዋል። እኛም የቀረበን ሁሉ ወዳጃችን እየመሰለን ተዘናግተን ሥንጠቃ ኖረናል፣ ከእንግዲህ ግን መዘናጋት አክትሟል። ዛሬ የእያንዳንድሽን መሠረትና ምንጭ ማጥናት ለአማራው ህልውና ጠቃሚ ሆኖ አግኝተነዋል።

(3) ሌላው <u>የነዓምን</u> ውሸት ደግሞ <u>ብዙ አማሮች የግንቦት ሰባት አባላት</u> አሉን፣ እዚህ ሥብሰባም ውስጥ ብዙ አማሮች አሉ ሲል መደመጡ ነው።

(4) <u>**ነዓምን**</u> ሥለዘመነ ካሴ ተጠይቆ፣ "ደህና ነው፣ አለ፣ መቼም የማይወራ ጉድ የለም" እያለ ቧርቋል፣" ትንሽ ሥለሚያመው፣ ከኤርትራ ወጥቶ እንደሚታከምም በአደባባይ ተናግሯል"።

-ይችን <u>ከኤርትራ ወጥቶ ይታከማል</u> የምትለዋን ንግግር ሕዝብ አድምጧታል። ማኖ ነክቷል ማለት ነው። ሥለዚህ ውጤቱን ጠብቀን የነዓምንን ዕውነትና ውሸት እንለየዋለን፣ ዕድሜ ይሥጠን። ሳያውቁት ወደኤርትራ የገቡ አማሮች፣ አንድ ጊዜ ኤርትራ

ከገቡና ቆራጥ ታጋዮች መሆናቸውን ሻዕቢያ ሲያውቅ ከፀረ-አማራነቱ የተነሳ፣ የቁም እሥር እንደሚያደርጋቸው እናውቃለን። እነተስፋዬ ጌታቸውን እንደገደለም እናውቃለን፣ እነ ኮሎኔል ታደሰን የቁም እሥር ካደረጋቸው በኋላ ዬት እንዳደረሳቸው አናውቅም።ሥለዚህ የዘመነ ካሴ ከዚያ የተለዬ ከሆነና ወጥቶ ሊታከም ከቻለ ደሥታውን አንችለውም።

ታማኝ በዬነም አማራው እየተሳደደ በሚገኝበት ወቅት፣ ልክ እንደ ነዓምን ዓይነት መልዕክት አሥተላልፏል። "ኦሮሞዎች ችግር አለብን ሲሉ አድምጧቸው። የባድመ ሁኔታም እንዲፈጠር እንደማይፈልግ ነግሮናል። በታማኝ በዬነ ከአማራ መወለድ ባልጠራጠርም፣ የሚስቱ ሁኔታ ወይም የልጁ መደባለቅ ሳይምታታበት አይቀርም፣ ምክንያቱም በዚህ በ26ዓመት ውሥጥ የአማራውን ያህል የተበደለ እንደሌለ እየታወቀ ሥለአማራው አንድ ነገር ሳይቆረቁረውና ሳይናገር፣ ለኦሮሞ ማረበዱ የጤንነት አይመሥልም። አንድ ሠው ከአማራ እናትና አባት መወለዱ ብቻ አማራ አያሰኘውም፣ለአማራ ቆሞ መታገል እንጅ።

# ኤፍሬም ማዴቦ

(1) ደግሞ እንደ ነዓምን ሥለአማራው "ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ" የሆነውን በውሸት የታጀበ ከንቱ ውዳሴውን እናድምጥለት "ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አገር ውስጥ ያለው ሥርዓት ከፋፋይ ነው በጎሳ አደራጅቶናል፣ በጎሳ ለያይቶናል፣ የጎሳ ፌደራሊዝም ፈጥሯል እያልን ለብዙ ዓመት እንጮህ ነበር። ያ ለብዙ ዓመት ይጮህ የነበረው ኃይል ነው ዛሬ ራሱን በጎሳ ማደራጀት የፈለገው። በተለይ በቅርብ ጊዜ የተነሳውና ያየነው ከአንድ አካባቢ ከአማራው ነው። ያ የሚያሳዬን በትግሉ ላይ ትልቅ ጠባሳ እንደሚያደርጉ ነው፣ ትግሉን ይጎዳል" ይለናል።

-"ለጥቂት ጊዜም ቢሆን"ብሎ ዓረፍተ ነገሩን ይጀምርና ዓረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ "ለብዙ ዓመት እንጮህነበር" ይላል። በአንድ ዓረፍተ ነገር "ጥቂትና ብዙ" ብሎ ቢያሥቀምጠውም፣ እንደገባኝ ከሆነ አማራው ወያኔን በጎሳ ሲወነጅል ኖሮ ለምን ጎሳን ይዞ ተነሳ ነው።

**ማዴቦ!** ራሱን መጠየቅና መመለስ የነበረበት "አማራው ብቻውን የኢትዮጵያ አንድነት እያለ 25ዓመት ሲታገል፣ሁሉም ጎሳዎች ከማዴቦ ጎሳ ጭምር በዘራቸው ተሰባስበው በአማራው ላይ ዱላ ሲያነሱና ሲያባርሩት ብሎም ሲገሉት ምን አደረግሁ፣ ተባባሪ ነበርኩ ማለት ነው" ብሎ ወደኋላ መለስ ብሎ ማሰብ ነበረበት። በነገራችን ላይ ማዴቦ ለራሱ ካልዋሸ ወይም ካለገመ በስተቀር፣ አማራው ለምን ዛሬ አምርሮ እንደተነሳ አያውቅም አልልም።

(2)! ቀጠል አድርጎ "ትግሉን የሚጎዳ ትልቅ ጠባሳ ነው" ይላል።

-ሥለየትኛው ትግል ነው ማዴቦ የሚያወራው? ይህንን አማራውን ከወያኔ ባልተናነሰ መልኩ ደቡቦች፣ኦነጎች ከኢሳያስ ጋር ሊያጠፉት የሚቅነዘነዙበትን ትግል ነው ወይስ ሌላ የማናውቀው ትግል አለ?

(3)! "በጎሳ ተደራጅተን አማራውን መከላከል አለብን"ብሎ የተነሳው ትንሽ ክፍል ነው፣ አብዛኛው የአማራ ተወላጅ አክላንድ እና ፐርዝ ያየሁት አልደገፈውም፣ ውድቅ አድርጎታል።

-የፖለቲካህን ውሸት ወደኋላ አቆዬውና ዕውነታው ገሀድና ከአንተም የተሰወረ ሥላልሆነ፣ በአማራነት የተነሳው ሕዝብ ብዛት አለው።

-"አክላንድ እና ፐርዝ የሚኖረው አማራ ውድቅ አድርጎታል" የሚለው አነጋገር ከዕውነት የራቀ የማዴቦ ፀረ-አማራ ምኞት ከመሆን አያልፍም። አክላንድ እና ፐርዝ የሚኖሩት አማሮች ውድቅ አደረጉት እንኳን ቢባል ጠቅላላ አማራን ሥለማይወክሉ

ምንም ማለት አይደለም። እንደትልቅ ነገር ይችን ከዕውነት ጋር የተጣላች ኢምንት ነገር አንጠልጥሎ መሮጥ፣ ለከሠረው የግንቦት ሰባት ፖለቲካ ትርፍ ያሥገኝ ይሆናል ተብሎ ታስቦ እንደሆን እርሱት።

(4)! "በኃሳ የሚደራጁ ሠዎች ትልቁ  የማያዩት ነገር፣ ለእነሱ የሚታገሉ እነሱ ብቻ ይመስላቸዋል። ሌላ ሠው ለምሳሌ እኔ ኤፍሬም ማዴቦ  ከእነሱ  እኩል  ለአማራው ሕዝብ ለመታገል ሙብት እንዳለኝና  መታገል እንደምችል ይረሱታል።

-አሁን ገና ማዴቦ አሾፈብን። አማራው መሬቱንና ሚስቱን እንዲሁም ልጁን ተቀምቶ 25ዓመት ሙሉ "አቤት፣ ይግባኝ" ሲል ኖሮ የሚደርሥለት ሲጠፋ ጫካ ገባ። ከዚያም ሆኖ ድረሱልን ወይም መሥሪያ ሥጡን ሲል የት ነበራችሁ ማዴቦ? ዛሬ የድል አጥቢያ አርበኞች ሆናችሁ የአማራውን ተጋድሎ ትግል የእኛ ነው እያላችሁ በአረብ ገንዘብ ዓለምን እየዞራችሁ ታጋይ መስላችሁ የቀረባችሁት። ደግሞስ በምን ተዓምር ነው አንተ ፀረ-አማራው ከምባታ፣ እየደማ ካለው ከአማራው እኩል ለአማራው ሕዝብ ልትታገል የምትችለው?

ከአማራው እኩል የምትታገል ከሆነም ደግሞ አማራው "በመኖርና ባለመኖር መካከል ነው ያለሁትና ለህልውናዬ መጠበቅ እየገደልኩ ልሙት፣መሰናክል አትሁኑብኝ" ሲል፣ "ከአንተ ጫካ ገብተህ ከምትፋለመው አማራ የበለጠ እኔ ሥለማውቅልህ፣ እኔን ተከተልና ሥልጣን አቆናጠኝ፣ ከዚያም በኦነግም ሆነ በአናሳዎቹ በእኛም ተረግጠህ ትኖራለህ " የሚል መልዕክት በተዘዋዋሪ ማሥተላለፍ ለምን አሥፈለገ?

የራሳችሁን አናሳ ኀሳዎችና ኦነግን እከክልኝ ልከክልህ እያላችሁና በአንቀልባ አዝላችሁ፣ የኢሳያስንና የእናንተን ፀረ-አማራነት ለመተግበር፣ ወያኔ ከሚያደርገው ባልተናነሰ መልኩ ልታጠፉት ሥትሯሯጡ ማዬት ምን ያህል ልብ ያደማል። አንተ ለአማራው እታገላለሁ ከምትል ይልቅ እንደመኸገር ተጣብቄ ከራሥህ አልወርድም ብትል ይቀላል። ከእንግዲህ እናንተንም ከወያኔ ለይተን ሥለማናያችሁ እርምጃ ከመውሰድ አናመነታም።

(5)! "በሶሻል ሚዲያ የሚጮሁት ጥቂት ሰዎች ናቸው። የአርበኞች ግንቦት ሰባት ብዙ የአማራ ተወላጆች አሉት።

በሶሻል ሜዲያ የሚታገሉት ብዙ እሳት የላሱ ጀግና አማሮች ናቸው። ግንቦት ሰባት ውስጥ ጥቂት አማሮች፣ብዙ  እናንተው ደቡቦችና ቅይጦች ብቻ ናችሁ። አማራው ዛሬ እናንተን ጨምሮ በጠላት ቢዋከብም፣ተራ በተራ ጠላቶቹን እያራገፈ፣በሂደት የሚያሸንፍ እንቅስቃሴ ነው የተጀመረው፣ ተስፋ አለኝ።ወያኔ ጋ እንደሚሞዳሞዱት ዓይነት ጥቂት አማሮች ግንቦት ሰባትም ውሥጥ አሉ፣ አንዳንዶቹም አማሮች ወደስደት ሲወጡ ባለማወቃቸው "ፈቃድ እናሰጣችኋለን" በማለት ግንቦት ሰባት አታሏቸው ተመዝግበው እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ ፈቃድ ሳያገኙ እያሥፈራሯቸውና በተለያዩ መንገዶች እየተጠቀሙባቸው በሥጋትና በባርነት የተቀመጡ ምሥኪኖች ናቸው።

<u>ከዚህ በተረፈ ከዛሬ ጀምሮ በግልፅ መነገር ያለበት ነገር ቢኖር ግንቦት ሰባት ውስጥ ብዙ አማራ ሳይሆን ብዙ እንደ አማራ አማርኛ ተናጋሪ ደቡቦችና ቅይጦች እንደሆኑ መታወቅ አለበት። አማራማ "አፍንጫ ሲመታ ዓይን ያለቅሳል" እንደሚባለው በአማራነቱ ተሰባስቦ ለገዛ ወንድምና እህቱ ህልውና ቆሞ በመታገል ላይ ነው።</u>

አንዳንድ  አማሮች የሆኑና ያልሆኑ ግን አማርኛ ተናጋሪዎች ከነዓምን፣ ከአበበ፣ ከጉራጌዎቹና ከምባቶቹ ከብርሀኑ፣ ከኤፍሬም፣ ከታደሰ ብሩ፣ ከገንዘብ ዘራፊው ሙሉነህ ኢዮኤል ጭምር "እኛም አማራ ነን፣ እነሱን ከእኛ የበለጡ አማራ ያደረጋቸው ማነው" ሲሉና ለአማራው ህልውና ቆርጠው የሚታገሉትን ሲያናንቁ ይሥተዋላሉ፣ ይደመጣሉም። በአሁኑ ጊዜ አማራነት የሚለካው ለአማራው በመቆምና በመታገል እንጅ ከአማራ ሥለተወለደ አለመሆኑን አይረዱም።ከአማራ ተወልዶ፣ የነገዱ ህልውና አፋፍ ላይ ሲደርስ ለዚያ ያልጮኸ አማራ፣ አማራ ነኝ ብሎ የሚያወራበት አንደበት እንዴት ሊኖረው ይችላል። <u>በመወለድ</u> ከሆነ <u>ጌታቸው ዳ</u> ትግሬ ነው፣ግን በአማራ ላይ የሚደረገውን ዓይን ያወጣ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሽንጡን ገትሮ ለዕውነት ሲቆም ያዩ ወያኔና ግንቦት ሰባት ውስጥ የተሸጎጡ፣ ትውልደ አማሮች ምን ይሰማቸው ይሆን?

አማራው ተጎዳሁ፣ የደረሰብኝን የጉዳቴን መጠን የማውቀው እኔው ራሴ ሥለሆንኩ፣ ለራሴ ህልውናዬ እኔው ራሴ እታገላለሁ ብሎ ሲወድቅ ሲነሳ፣ ጉራጌው ብርሀኑና ከምባታው ኤፍሬም ማዲቦ እኛ እናውቅልሀለን የሚል ድፍረታቸው ምን ያህል አማራውን ቢንቁት ነው፣ ለሰሚውስ አይገርምም?

# ክፍል 4

## <u>አበበ ቦጋለ</u>

በማርች 5 2017 ዩ ቱብ ላይ እንደተደመጠው፣ አበበ ቦጋለ ደግሞ ሥለዘመነ ካሴ ተጠይቆሲመልስ፣ ዘመነ ካሴ አለ፣ እጁን ተሰብሯል። ወደፊት ወጥቶ እንዲታከም እየተሞከረ ነው። ወደዚያ ትግል ሲገባ እኮ መሞትም እንዳለ አውቆ ነው፣ የሄደው። ከቤልጄም የሄደውና የተሰዋው ገብርዬ ከዘመነ ካሴ ይበልጥ ታዋቂ ነበር። ሥለ ዘመነ ካሴ የሚናገሩ ሰዎች ለዘመነ አሥበውና ተቆርቁረው ሳይሆን የአማራን ብሔርተኝነት ለማራመድ የእሱን ነገድ ምክንያት ይፈልጉታል።

<u>**አበበ**</u>! ሥለ ደሚትም ሲጠየቅ፣ ደሚትን የወያኔ ባከ አፕ አድርጌ አላየውም። ለምን ወያኔ ደሚትን በሽብርተኝነት አልፈረጀም ሥላላችሁኝ፣ እሱን እንደወያኔ ሆኖ መመለስ አይቻልም፣ ግን ዝም ብሎ ለተመለከተ ሠው እንኳን አሸባሪ ብሎ ሊመድባቸው <u>ተቃዋሚ አድርጎ እንኳን አይገልፃቸውም፣ ምክንያቱም የትግራይ ሕዝብ ከራሱ የወጣ ጠበንጃ የታጠቀ፣ ህዋሀትን የሚታገል ኃይል መኖሩን እንዲያውቅ ወይም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቅ ከሆነ፣ የትግራይን ሕዝብና ወያኔን ለይቶ ማዬት ሥለሚችል፣ ያ ደግሞ እነሱን በትግራይ ሕዝብ ሥም የትግራይን ሕዝብ የሥልጣናቸውን ማሥቀጠያነት እንዳያበላሽባቸው ሆን ብለው ሰፕረስ የሚደብቁት ይመስለኛል።</u>

**ትችት**! አንባቢዎች ከላይ የተሠመረበትን የአበበን ንግግር ደጋግማችሁ ካነበባችሁት ወያኔና ግንቦት ሰባት የሚያምታቱት የአማራ ተጋድሎዎች ትግል ቁልጭ ብሎ ይታያል። ታዲያ ወያኔ በደሚት ላይ የሚያደርገውን አበበ ከዚህ በላይ እንደገለፀው መሆኑን እያወቀ፣ ወያኔም የአማራ ተጋድሎ በትጥቅ እዬተጋፈጠ የሚያሥመዘግባቸውን ድሎች በሌለበትና ባልዋለበት ግንቦት ሰባት ነው ሲል፣ እነ አበበም የአማራ ተጋድሎን ትግል ለመደበቅና የግንቦት ሰባት ለማስመሰል "የነፃነት ኃይሎች" ከዚያም ባሻገር "ብአዴን የላካቸው የሶሻል ሚዲያ ሠራዊት" እያሉ ለምን ይዋሻሉ?

### ከዚህ በታች የሠፈረውን በዝርዝር ያቀረብኩበት ምክንያት ብዙ እርስ በእርሱ የሚቃረኑና የሚምታቱ ጉዳዮችን ከመጠን የለሽ ውሸት ጋር ሥለታጀቡ ጠቅለል ባለመልክ ለማቅረብ ሥለተቸገርኩ ነው።

**አበበ ቦጋለ!** የግንቦት ሰባት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ተብዬው ቃለ መጠይቅ በኢትዮ ቲዩብ የሱፍ ኢብራሂም ጠያቂነት፣

(1) **ጠያቂው!** የኤርትራን መንግሥት አምናችሁ ነው የገባችሁት በወቅቱ?ማንን ተማምናችሁ ገባችሁ?

**አበበ!** ራስን የመከላከል ኃይል ለማደራጀት፣ ወያኔ አምበርክኮ ልግዛህ ሲል ኖ ለማለትም ቦታ ያሥፈልግሀል። ኢርትራ ሰዎችን የምናሰለጥንበት ቦታ ይሰጥሀል። ኤርትራ ላይ ያለው ጠላትነት ደግሞ ትክክል አይደለም ምክንያቱም ኤርትራና ኢትዮጵያ በታሪክ፣ በባህል፣ በቋንቋ፣ በሥነልቦና አንድ የሆኑ ለረጅም ዓመታት ያንድነት ታሪክ ያላቸው አገሮች ናቸው። ነፃነቷን ኤርትራ ነፃነቷን ያገኘችው የዛሬ 26 ዓመት ነው ከዚያ በፊት በጣሊያን ቅኝ ሥር ሆነውም እንኳን ለአገራቸው ፍቅር የከፈሉት መሥዋዕትነት በታሪክ ተመዝግቦ ያለ ነው። ሥለዚህ ያ ዕይታ ኤርትራን እንደጠላት፣ ኤርትራን እንደሥጋት ለማዬት የተደረሰበት ደረጃ ራሱ ትክክል አይደለም፣ ምክንያቱም የፖለቲካ ኤርትራውያኖችንም ለመሳሪያ ትግል ያነሳሳቸው በቂ

ምክንያት አለ። የፌደሬሽናቸው መፍረስ ነው። ያ ፌደሬሽን መፍረስ ያልነበረበት መሆኑን ማንም ኢትዮጵያዊ ፖለቲካ በዕውነት የሚያይ ሰው ሊያረጋግጠውና ሊቀበለው የሚችል ነው። ያ ፌደሬሽን በመፍረሱ ምክንያት ደግሞ ወደጦርነት የተገባበት ነበር፣ ሁለቱንም አገሮች እንዳልጠቀመ ታይቷል።

**ትችት!** አበበ! ኢሳያስ ያኀረሰውን የውሸት ተረት ተረት ሲያቀረሽብን ታዘቡት።

(2) **ጠያቂው!** *መጀመሪያ ኤርትራ ሥትገቡ፣ ቦታ እሥኪፈቅድላችሁ፣ ምን ነበር የኤርትራ ፍላጎት ወይም የሁለታችሁ የኤርትራና የግንቦት ሰባት ሥምምነት?*

**አበበ!** *እኛ ከኤርትራኖች ጋር የተነጋገርነው አገራችንን ነፃ ለማውጣት እንፈልጋለን፣ ወያኔ አገራችንን ለመበታተን የሚሠራውን የፖለቲካ ሥራ ታውቃላችሁ፣ አገራችን ከአሁን በኋላ ዲሞክራታይዝ ካልተደረገች በሥተቀር የመበታተን አደጋ አለባት፣ ሥለዚህ አገራችንን ነፃ ለማውጣት የምናካሂደው ትግል ደግሞ አገር ውስጥ ሆነን የሞከርነው ሥራ በወያኔ ተጨናግፏል፣ ያንን የተጨናገፈ ጥረት እንደገና መልሶ እንዲያንሰራራ ለማድረግ የጉልበትም ሥራ መታከል አለበት። ሥለዚህ እናንተ አገር መጥተን በሙሣሪያ ኃይል ለመደራጀት ቦታና ዕርዳታ እንፈልጋለን ነው። በዚያ ሁኔታ ነው። እነሱም ደግሞ ጥቅም አላቸው፣ ወያኔ ሥልጣን ላይ ከመጣ ጀምሮ በኢትዮጵያና በኤርትራ ውስጥ የቆየውን ታሪካዊ ግንኙነት ሊያበላሽ በሚችል መንገድ ከጦርነቱ በኋላ በባድመ ላይ ጦርነት ከገቡ በኋላ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ያለውን ቦርደር (ወሰን ለማለት ፈልጎ ይመስላል) በመዝጋት ጭምር <u>ታይቶ የማይታወቅ ጠላትነትን</u> በዚያች ምድር ያሰፈሩ፣ በሁለት ሕዝቦች መካከል የጋረጡ ብቻ ሳይሆን፣ ከዚያም ባለፈ በዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ኤርትራ እንድትገለል ለምዕራባውያን መሥሪያና አሽከር በመሆን በኤርትራ ላይ ከፍተኛ ወንጀል የሠሩበት ሁኔታ አለ። በሀሰት እየከሰሷቸው፣ "ኤርትራ አልሸባብን ትደግፋለች፣ አልሸባብን ታሥታጥቃለች" ሶማሊያ ውስጥ ላለው ችግር ኤርትራ ተጠያቂ ነች የሚል አንዳንድ ጊዜ የፈጠራ ዳታዎችን ለወዳጆቻቸው እየሰጡ ኤርትራን ከፍተኛ ማዕቀብ ውስት የከተቱና ኤርትራ ከዓለም አቀፉ ህብረተሰብ እንድትገለል ከፍተና ጥረት አድርገዋል። ሥለዚህ ለእነሱም ለ እኛም የጋራ ጠላታችንን ወያኔን በማስወገድ ወያኔ ከወረደና ከጠፋ በኋላ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ታሪካዊ ወንድማማችነትና ግንኙነት ሁለቱን አገሮች ሊጠቅም በሚችልበት መንገድ ላይ ማምጣት ሁለቱንም አገሮች እንደሚጠቅም ያውቃሉ እኛም እናውቃለን።*

**ትችት!** ለኢሳያስ የቀረበው ማመልከቻ "አገራችን ዲሞክራታይዝ ካልተደረገች የመበታተን አደጋ ሥለሚገጥማት ቦታና እርዳታ ሥጡን" ነው ባጭሩ። ኢትዮጵያን የበተኗት ዋኖቹ እነ ኢሳያስ፣እነመለስና እነኦነግ ሆነው ሳለ፣ ኢሳያስን እንደገና የቀረውን አፍርስ ለማለት ካልሆነ በሥተቀር ምንም ውጤት እንደማያመጣ ግልፅ ነው። ኦነግንም በሀገራዊ ንቅናቄ ተብዬው መሸጎጥ ውጤተቢስ ነው። ሌላው አበበ በድጋሜ የኀረሰውን የኢሳያስ የውሸት ተረት ተረት እንደገና ሲያቀረሽብን ታዘቡት። የእነማን ጆሮ ይሰማል ብሎ ነው፣ እንደ ውሻ በበላበት የሚጮኸው?

(3) **ጠያቂው!** *ፎከስ (focus) እናድርግ፣ የጦር መሣሪያ በተባለው ላይ ዕድገቱ እንዴት ነው? ውጤቱስ እንዴት ነው?*
**አበበ!** *እምልህ እኮ ምን መሰለህ፣ ይከ ጦርነት አይደለም። የጦር ድርጅት አድርጎ ማቅረቡ አየህ! ጦርነት ተከፈተበት። ወያኔ ተቃዋሚዎች ላይ ጦርነት ከፍቷል። ያን ጦርነት የምትከላከልበት ኃይል ማደራጀት አለባቸው። ሥለዚህ ጦር አይደለም ራሱን የሚከላከል ኃይል ነው።*

(4) **ጠያቂው!** *ግንቦት ሰባት የተቋቋመው በ2008 ዓ.ም ነው። 8 ዓመት አልፎታል። ረጅም ነው። 8 ዓመት አቶ አበበ፣ እንደምሳሌ እንኳን መጥቀስ ቢቻል ህዋሀት በ8 ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ የራሱ ነፃ መሬት ነበረው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር የሚንቀሳቀሰው፣ ይኸ 8 ዓመት ምን ይመስል ነበር?*

**አበበ!** *ወያኔና ግንቦት ሰባትን ካነፃፀረ በኋላ "እሱ አይደለም ቁም ነገሩ ግን ላለፉት 8 ዓመት ንቅናቄያችን ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ሥራ እየሠራ ያለው፣ ይህንን የወያኔ ሜዲያ ብትከታተል መለስ ዜናዊ ከመሞቱ በፊት ምክር ቤት (ፓርላማ) ውስጥ ቁጭ ብሎ "ግንቦት ሰባት እዚህ መሀከላችን አለ" ብሎ ሲናገር ሥምተኸዋል። መፈንቅለ መንግስት ወያኔ ያደረጉት ሠዎች በግንቦት*

ሰባትነው ተከሰው ከርቸሌ የወረዱት።

**ትችት!** ወያኔ ራሱ ዋሾ ሥለሆነ ግንቦት ሰባት አፍና ምላስ እንጅ ፋይዳ እንደሌለው፣ በጎምነፋ፣ በወልቃይት ወያኔዎችን እረፈረፍኩ እያለ የለፈፈውን ውሸት መሆኑን ጠንቅቆ ያውቀዋል። ወያኔ የብርሀኑን የምላስ ፕሮፓጋንዳ በሽብርተኛ ሥም፣ መፈንቅለ መንግሥቱንም ሳይኖርበት የግንቦት ሰባት እያለ ቢጠቀምበት፣ ገንዘብ ከምዕራቡ ዓለም ለመሰብሰብ እንደሚያሥችለው ሥላወቀ የተጠቀመበትን መንገድ ሲሆን፣ ዋሾው አበበ! "መለስ ዜናዊ ከመሞቱ በፊት ምክር ቤት (ፓርላማ) ግንቦት ሰባት እዚህ መሀከላችን አለ" ብሎ ተናግሯል ብሎን አረፈው። ይች ናት ትግል።

(5) **ጠያቂው!** ምን ያህል ነበር የግንቦት ሰባት እጅ በኩዴታው?

**አበበ!** የግንቦት ሰባት እጅ ይህን ያህል ነው ብዬ እኔ ከምነግርህ ይልቅ ወያኔ የሰጠውና የተጠቀመውን መረጃነት ክስ ኢምፖርታንት ይመስለኛል። እኔ እንደ ግንቦት ሰባት አባል ዛሬ በዚያን ጊዜ ሥለነበረው ይህን ያህል ነበረ ተሳትፎው ማለቱ የሚጠቅም አይደለም። ወያኔ እኮ ሙሉ በሙሉ የግንቦት ሰባት ኦፐራሽን ነው ብሎ በገሀድ ተናግሯል።

(5) **ጠያቂው!** አቶ አበበ መፈንቅለ መንግሥቱ ላይ የግንቦት ሰባት ኃላፊነት ምን ነበር?

**አበበ!** እሱ አሥፈላጊ አይደለም። ነገርኩህ እኮ፣ ወያኔ የሰጠው መንግሥት፣ ወያኔ መንግሥት ነው።

(6).**ጠያቂው!** ግን እናንተስ ኢንቮልቭ(ተሳትፈናል) ብላችሁ ታምናላችሁ?

**አበበ!** ምን ያሥፈልጋል ዋናው ነገር አገር ውስጥ ነው ያለነው፣ አገር ውስጥ እየሠራን ነው ያለነው። ይህን ነገር በወቅቱ የነበረው ጠቅላይ ምኒስቴር ተናግሯል፣ አሁንም በየጊዜው ብትሰማ ዋልታን፣ሪፖርተርን፣ ኢንፎርሜሽን ማዕከልን፣ የኢትዮጵያን የዜና አገልግሎት ብትመለከት እያንዳንዱ ዛሬ ድረስ የግንቦት ሰባት አሰልጥኖ የላካቸው፣ አብረው ሲሰሩ የነበሩ እየተባሉ በርካታ ሠዎች ይታሠራሉ።

**ትችት!** እንደ አበበ መልስ ከሆነ፣ የግንቦት ሰባት የትግል ምሥክሮች፣ መለስ፣የወያኔ ዋልታ፣ ሪፖርተር፣ ኢንፎርሜሽን ማዕከል፣ የኢትዮጵያ የዜና አገልግሎት ናቸው።

(7)**ጠያቂው!** ተፈርዶባቸው ክሱ አልቋል፣ ቢነገር ምን ያመጣል?

**አበበ!** እነሱ ብቻ አይደለም፣ ከዚያም በኋላም ቀጥሏል፣ እሱ ብቻ አይደለም ከመፈንቅለ መንግሥቱም በኋላ

(8)**ጠያቂው!** የተጠጋ ነገር ሥለሆነ አሁን ብናወራው ምንም ችግር የለውም ብዬ ነው አቶ አበበ?

**አበበ!** ኖ ችግር አለው፣ ዝምብለህ፣ አይጠቅምም፣ ችግር ባይኖረውም፣ ዕውቀት አይጨምርም፣ ምክንያቱም ፎርግራንት ተወስዷል። እነኚህ ሠዎች ከግንቦት ሰባት ጋር ይሠራሉ ተብሎ ወያኔ አለኝ በሚለው መረጃ ይህንን አረጋግጫለሁ ብሎ ሠዎቹ ላይ የዕድሜ ልክ እሥራት ፈርዷል።

(9) **ጠያቂው** አሁንም አጥብቆ ይጠይቃል! እሱ የመንግሥት ነው አቶ አበበ፣ እኔ ግን ጥያቄዬ ይቅርታ የግንቦት ሰባት፣ እንደውም እኔ የሰማሁት የአማራ ተወላጆችም አሉበት ነው፣ግን?

**አበበ!** ይኸውልህ ምናለ መሰለህ የአማራ፣ የኦሮሞ ብለህ የምታየው አይደለም። የግንቦት ሰባት አባላት አማራም፣ ትግሬም፣ ወላይታም፣ ኦሮሞም 80 ብሔረሰብ ሊሆን ይችላል። አባል ሲሆኑ በኢትዮጵያዊ ማንነታቸው ነው። ሥለዚህ ተዋናዮቹ

አማሮች ወይም ጉራጌዎች ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህንን ተግባር የፈፀሙት አማሮች ሥለሆኑ የአማሮች እንቅሥቃሴ ነው ማለት አይደለም።

**ትችት!** የምናውቀውን ሀቅ ሲክዱን መለስ ብለው ደግሞ አብረን እንታገልና ወያኔን እናስወግድ ሲሉ መተማመን እንዴት ይቻላል? "ማን ይናገር የነበረ፣ማን ያርዳ የቀበረ" ነውና በጉዳዩ የነበረበት ኮሎኔል አለበል አማራ በድል በአንድነት ራዲዮ ግንቦት ሰባት ገንዘብ እንዲረዳ ከተጠየቁት እርዳታ ሠጭዎች መካከል አንዱ ሥለነበር ገንዘብ እረድቷል። ከዚህ ውጭ ግን ከአሠራር እሥከ ምሥጥር እንደሌለበት ተናግሯል።

እኛም እሥከናውቀው ደረስ ግንቦት ሰባት ሳይተኩስ እንደተኮሰ፣ ሳያደርግ እንዳደረገ የበሬ ወለደ በሽታውን ጠንቅቀን ሥለምናውቅ አልተቀበልነውምና። አበበም ከእነ ድርጅቱ በውሸት ላይ ተነሥቶ በውሸት ካሰብኩት እደርሳለሁ ብሎ ሲኳትን ማጣፊያው ቸግሮት። ኮሎኔል አለበል አማራ ዕውነቱን አሥጨብጦናል። ልብ ያለው ልብ ይበል።

(10) **ጠያቂው!** እንደውም እኮ አቶ አበበ አንድ ሌላ ክስ ተያይዞ የሚመጣው፣ ለመከሸፉ ዋናው ምክንያት ከሁለት ወር በፊት የግንቦት ሰባት አመራሮች ወጥተው በቴለቪዥን የአርበኞች ጥሪ በ6 ወር ውስጥ ኢትዮጵያ እንገባለን በሚል **500 500 ዶላር** የሰበሰቡበት ወቅት ነበር። አንዱ እንደውም ለመንግሥት በወቅቱ ምልክት የሠጠው ይኸ ንግግር ነው ተብሎ ይወነጀላል?

**አበበ!** ውንጀላ ሁል ጊዜ አለ። ነገር ግን ምንድነው መሰለህ፣ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ዕቅድ ይኖርሀል ሁልጊዜ።

**ትችት!** የግንቦት ሰባት ልሳን የሆነው ኢሳት ኀቤ መልኬን ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ ፎቶውን በዩቱብ ለቆ ማስገደሉን ውንጀላ እንደማይለው ተስፋ አለኝ።

(11) **ጠያቂው!** ሥድስት ወር ሲባል ምንን ተንተርሶ ነው?

**አበበ!** በዚያን ሰዓት ላይ በሥድስት ወር ጊዜ ውስጥ የፖለቲካ ትግሉን ለማጠናቀቅ የሚያሥችል ፕላን ነበር። ምናልባት ፕላኑስ መፈንቅለ መንግሥት ሆኖስ ከሆነ ብለህ አሥብ ዝምብለህ (ካፍርኩ አይመልሰኝ ሆነብኝ) ጠያቂው ለመጠየቅ ሲታገል አበበ ማጣፊያው ሥለቸገረው፣ በውሸት ሳቅ ታጅቦ እየጋገመ" ሆኖስ ከሆነ"ብለህ አስበው፣ "ሆኖስ ከሆነ" ብለህ አስበው ማለቱን ቀጠለ። ግን በዚያ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ወያኔ ይህን መፈንቅለ መንግሥት አከሸፍኩ አለ። በዚያ መፈንቅለ መንግሥት ውስጥ ድርጅታችን ተሳታፊ ነው ብሎ በመሪዎቻችን ላይ የሞት ፍርድ ፈረደ። የሞት ፍርድ በተፈረደበት ጉዳይ ላይ ማስተባበያ መሥጠቱ ጥቅም የለውም።

**ትችት!** ሲያምታታ ተከታተሉት

(12) **ጠያቂው!** እኔ እንዲነሳ የምፈልገው ሁለት መፈንቅለ መንግሥት በሥነ ሥራት ተደርገው በታሪክ የተቀመጡ አሉ። ይኸ ግን 3ኛ ያልተነገረ፣ የተድበሰበሰ ጉዳይ ነው። እና መረጃዎች ነበሩ፣ አቶ አንዳርጋቸው ፕሮፌሰር ብርሀኑን ጨምሮ ዱባይ ድረስ ሄደው ከትግሉ ጋር ተገናኝተዋል በሚል በመረጃ ደረጃ የቀረበበት ሁኔታ ነው ያለው፣ ይህንን?።

**አበበ!** አየህ መለስከው። ብርሀኑና አንዳርጋቸው ዱባይ ድረስ ሄደው መፈንቅለ መንግሥቱን ያካሄዱት ሠዎች ጋር ተገናኝተዋል የሚለውን መረጃ ከተቀበልክ፣ እኔ ቅድም ያልኩትም ይኸ ነው፣ ወያኔ ማሥረጃ አለ ብሎ ፈርዶባቸዋል በእነዚህ ሠዎች ላይ።

(13) **ጠያቂው!** ማሥረጃውን ያረጋግጡልኛል ወይ?

**አበበ!** የእኔ ማረጋገጥ አሥፈላጊ አይደለም። ጊቭን የሆኑ ነገሮች አሉ። አሁን ለምሳሌ ያ ጥረት ከሸፈ።

(14) **ጠያቂው!** ለምን ከሸፈ?

**አበበ!** *መክሸፉ በጣም የሚያሳዝን ነገር አለው፣መክሸፉ ይህን ሁሉ ሥቃይም ሕዝቡ ላይ አመጣ ግን እንደማስበው ተዋናዮቹ በሚገባ ያላጠናቀቁትና መሥራት የነበረባቸውን ሳይሰሩ የቀሩት ሥራ ያለ ይመሥለኛል። በዚያ ምክንያት ለመክሸፍ ችሏል ብዬ አስባለሁ።*

**ትችት!** በቅጥፈትና በውሸት እሥከመቼ መጓዝ ይቻል ይሆን አበበ ብርብራው?፣

(15) **ጠያቂው!** በኦሮሞ ተወላጆችና እንደዚሁም በአማራ ክልል ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ይኸ እንግዲህ 5 ወር አለፈው፣በዚያ ላይ የአርበኞች ግንቦት ሰባት እንቅስቃሴ የሚታይ እንደውም ከመግለጫ የዘለለ ሥራ ሲሰራ አልታዩም ተብሎ ይወነጀላል፣ እንደውም ገና ትግል መቼ ጀመረ የሚሉ አሉ?

**አበበ!** *መታወቅ ያለበት ትኩረቱ ዋናው ጠላት ላይ ሳይሆን በፖለቲካ ድርጅቶች መሀል እንዲሆን ወያኔ አሰልጥኖና ደመወዝ ከፍሎ በሽህዎች የሚቆጠሩ "የሶሻል ሚዲያ ሠራዊት" ማሰማራቱን ከሁለት ዓመት በፊት በማስረጃ ተናግረናል። ግንቦት ሰባትና ኢሳት ላይ እየዘመቱ፣ የአማራን ሥም የሚያነሱ ሰዎች ወያኔ ያሰማራቸው "የሶሻል ሚዲያ ሠራዊት አባላት" እንደሆኑ እናውቃለን <u>መረጃ</u> ሥላለን እኮ ነው ይህንን የምነግርህ።እንደውም እኛን ዝቅ ለማድረግ (አንደርማይን) የተጀመረውም ከዚያ በኋላ ነው።*

(16) **ጠያቂው!** በአለፈው አራት ወር አካባቢ በአማራነት ከተደራጁና እንዲሁም ከግለሰቦች ጋር ግንቦት ሰባት ትልቅ ቅራኔ ውስጥ ገብቷል፣ምንድነው ምክንያቱ?

**አበበ!** *"ቅራኔ ውስጥ ገብቷል ለማለት ሁለት ወገኖች ማለትም ግንቦት ሰባትና ሌላ ወገን መኖር አለበት" ካለ በኋላ "ቅድም ያልኩት ነው፣ ይህንን የምልህ <u>መረጃ</u> ሥላለኝ ነው።*

**ትችት!** አበበ በቀጥታ ለመናገር ድፍረቱን ሥላጣ ነው እንጅ ሊዋሸና ሊክድ የፈለገው የአማራ ተጋድሎ የሚባል ትግል የሚያካሄድ የለም፣ ያሉት ቅድም እንዳልኩህ ወያኔ ያሰማራቸው የሶሻል ሚዲያ ሠራዊት ሥለሆኑ ከማን ጋር ቅራኔ እንገባለን ነው። ዓለም ያወቀውን ፀሐይ የሞቀውን የአማራ ተጋድሎ፣ ልክ እንደወያኔ ግንቦት ሰባትም ሊክድና ዕውቅና ላለመሥጠት ዙሪያ ጥምጥም መሄዱ ቅራኔውን ያሰፋዋል እንጅ አያጠበውም። የአማራውን ትግል ሙሉ በሙሉ ከተቀበለ፣ ፈረንጆቹ ከውያኔ ጋር እሥኪያማልዱት ድረስ ጊዜ መግዣ ሥለሚያሻው በአካባቢያችን እንዲቀላውጥ እንፈቅድለታለን።
አለበለዚያ ግን እንዲሁ ሳይገድል ገድያለሁ፣ሳይማርክ ማርኬያለሁ እያለ 8 ዓመት እንደዋሸው ከቀጠለ ላይ ታች ሲል ውድቀቱን ያፋጥናል።

(17) **ጠያቂው!** <u>መረጃ</u> አለኝ ብለዋልና እነማናቸው? ብሎ አጥብቆ ይጠይቃል።

**አበበ!** *እነገሌ እነገሌ ብዬ ልነግርህ አልፈልግም። በወቅቱ በነበሩበት <u>ብአዴን</u> ውስጥ ወያኔ አሠልጥኖ ባለፈው 2ዓመት ወደፈረንጅ አገር የላካቸው በሽህዎች የሚቆጠሩ ናቸው። የአማራውን ኮዝ አድቮኬት የሚያደርጉ መስለው (የአማራውን ሁኔታ የሚያሥተጋቡ መስለው) "በወያኔ ላይ ብቸኛው ሥጋት ፈጣሪ ግንቦት ሰባት ሥለሆነ፣በአማራ አካባቢ የሚተላለፍበትንና አማራን መሠረት የሚያደርግበትን ጥረት ካበላሸነው ሥጋታችን ይቀንሳል፣ቀሪው የፖለቲካ ሥራው ሥለሆነ መቋቋም እንችላለን" ብሎ ወያኔ ያወጣውን እሥትራቴጂ አሥፈፃሚዎች ናቸው።*

**ትችት!** "በወያኔ ላይ ብቸኛው ሥጋት ፈጣሪ ግንቦት ሰባት ሥለሆነ" ብሎን አረፈው፣ አለማፈሩ፣ በወሬ ነው ሥጋት የሚፈጥረው። መታገል ሲያዳግት "የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ" በሚል ዘይቤ ምላስን በመጎልጎልና ጣትን በመቀሠር ግንቦት

ሰባትንና ኢሳትን መቃወም ማለት ወያኔ በብአዴን መልክ ከ2 ዓመት በፊት ላካቸው ለተባሉት አማራዎች እንደማስረጃ ሊቀርብ ይችላል ወይ?

በማድበስበስ ጫካ የገባውን  የአማራን ተጋድሎ ወያኔዎች ናቸው፣ ውጭ አገር የተሰደዱትን አማሮች ወያኔ እንዳሰማራቸው ሠላዮች "የሶሻል ሚዲያ ሠራዊት አባላት" ብሎ የአማራውን የማንነትና የህልውና ታጋዮች ለመሳደብና ለማሳነስ  የሚደረገው ከአፈርኩ አይመልሰኝ ቅጥፈት መረን ለቀቀ ።

(18) **ጠያቂው!** ምናልባት አቶ አበበ እንደዚህ የተለዬ ሀሳብን ይዘው የሚመጡ ሠዎችን "ወያኔዎች" ማለት አይከብድም?" ብሎ ይጠይቀዋል።

**አበበ!** የተለዬ ሀሳብ መያዝና  ጠላትን መለዬት አለመቻል  የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የተለየ ሀሳብ ማለት "ግንቦት ሰባት እንዲህ ማለት ነበረበት፣ እንዲህ እንዲህ ማድረግ አለበት፣ መግለጫው ትክክል አይደለም ወዘተ ማለት ነው፣ እንጅ  ግንቦት ሰባትንና ኢሳትን መቃወም አይደለም"።

**ትችት!** ግንቦት ሰባትንና ኢሳትን መቃወም ማለት ወያኔ በብአዴን መልክ ከ2 ዓመት በፊት ላካቸው ለሚላቸው አማራዎች እንደማስረጃ ሊቀርብ አይችልም። በመጀመሪያ ደረጃ ወያኔ ከራሱ ትግሬዎች  ውጭ ሌላ ዘር በተለይ አማራን ለሥለላ ወደውጭ እንደማይልክ ዓለም ያወቀው ሀቅ ሆኖ ሳለ፣ምንም እንኳን አበበ ዕውነትን  ባያውቃትም፣ የዋሆቹ ሳይጠራጠሩ እንደለመዱት እንዲከተሏቸው አሥመሥሎ ቢዋሽ ምን ነበረበት።

(19) **ጠያቂው!** አማሮች በፖለቲካው ጠንከረው እንዳይወጡ ፕሮግራም ቀርፆ እየሠራ ነው የሚል ውንጀላ ያቀርባሉ፣እንዴት ያዩታል?

**አበበ!** ነዓምን "እኔ አማራ ነኝ፣ ሥንት አማሮች አለን ብሏል።

**ትችት!** የአይጥ ምሥክሯ ድንቢጥ። መቼም ቅል ግጥሙን አያጣም።

(20) **ጠያቂው !** ሥራ አሥፈፃሚው ውስጥ ሥንት አማሮች አሉ?

**አበበ!** ይኸውልህ ሥራ አሥፈፃሚ ውስጥ ሥንት ሠዎች አሉ ብትለኝ ይሻላል? ይለዋል።

(21) **ጠያቂው!** መነሻው... ብሎ ሲጀምር አበበ አቋረጠውና የራሱን እንዲህ ይቀጥላል።

**አበበ!** ሥራ አሥፈፃሚ ውስጥ 10ናቸው። ከ10ሩ ውስጥ እኔ እሥከማውቀው ድረስ አማርኛ አፍ መፍቻው ያልሆነ 1ወይም 2 ሠው ነው የማውቀው።

(22) **ጠያቂው!** ጥያቄው "አሁን እያወራን ያለነው፣ ብዙም ተቃውሞ የመጣው ከአማሮች ነው እያልኩ ነው። ሥራ አሥፈፃሚ ውስጥ ምን ያህል የአማራ ተወላጆች አሉ? ይህንን ነው፣ እሱ ነው መነሻው" በሚል በሥጨት ብሎ በድጋሜ ጠየቀው።

**አበበ!** መልሼ ነገርኩህ እኮ! ቋንቋን እንደብሔር መለኪያ ከለካኸው.......

**ትችት!** አበበ  ያልጠበቀው ጥያቄ  ሳይሆን አይቀርም፣ከድንጋጤው የተነሳ ከንፈሩ ሲንቀጠቀጥ፣ዓይኑ ሲፈጥና ዕጢው  ዱብ ሲል ተሥተውሏል።

**(23) ጠያቂው!** አማራ የሚባል ብሔር የለም እያሉኝ ነው? በሚል በአርምሞ እየተመለከተ፣ በመገረም አሥረግጦ ይጠይቀዋል።

**አበበ!** ማጣፊያው ቸግሮት ሁለት እጆቹን እያፍተለተለ እንዲህ ሲል ይመልሳል፣" ኖ ሠው ራሱ አማራ ነኝ ማለት ይችላል.....

**(24) ጠያቂው!** ኦሮሞ ተሰብስቦ ግን የኢትዮጵያ ድርጅት ነው ቢል እሥቲል...፣ ግን ቅድም እንዳልከው በስሜት ግን ደስ ሥለማይል፣

ከተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ማለትም ከኦሮሞ፣ ከጉራጌ ከአማራ ወዘተ.... ተመርጦ ፓርቲ የሚቋቋመው ለምን ይመስለወታል? ብሎ ይጠይቀዋል።

**አበበ!** የሚመስለኝ፣ የአገራቸውን ፖለቲካ በብሔር ማንነት ላይ ያዋቀሩ አገሮች ናቸው።

**ትችት!** እንዲህ ዓይነት ገልቱ መልስ ደናቁርቶቻቸውን የሚያታልሉበት አዲሱ የአበበ ግኝት ነው።

አበበ ቀደም ብሎ ስለተጠየቀው ሲሙለጨለጭ ቆይቶ እንደገና ወደኋላ ተመልሶ ለጠያቂው መልስ ልሥጥ ሲል መናዘዝ ጀመረ! "የቅድሙ ሥንት አማራ አለ ያልከውን ግልፅ ላድርግልህ ከ10 ሥራ አሥፈፃሚ ውስጥ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ከ2 እና ከ3 አይበልጡም" ብሎ አቀረበ።

**ትችት!** ቀደም ሲል በተራ ቁጥር (21) 1 እና 2 የነበሩት፣ አሁን ደግሞ በተራ ቁጥር (24) 2 እና 3 ሆነዋል። ቆዬት ብሎ ደግሞ ውሸት ማለቂያ ሥለሌለው 3 እና 4 እያለ ሽቅብ መሄዱ አይቀሬ ነው። ቅብጥርጥር ይብቃ። አማራ የለም ነው መልሱ። መወሻከት አያሥፈልግም። ኤቲክና ሞራል የሚባሉትን አታውቋቸውም?

**(25) ጠያቂው!** የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ በሚለው ውስጥ የኦሮሞ፣ የአፋር የሲዳማ የአማራ ብዙ ሥለሆኑ ወደፊት እናካትታለን ብላችኋል ወዘተ ብሎ ይጠይቃል።

**አበበ ቦጋለ!** የቆጡን የባጡን ከተናዘዘ በኋላ፣ "በጣም ክብርና ዕውቀት ያላቸው እነ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን የመሰሉ ሰዎች እንኳን ባደራጁት ድርጅት ውስጥ እኔ ወርጄ በአማራነት አልደራጅም፣ ይኸ ወያኔ አገራችንን ለመበታተን የፈጠረው የፖለቲካ ሥልቻ ውስጥ አንገባም" ብሎ ነበር። ኢትዮጵያዊ ነን ብለው የኢትዮጵያን አንድነት ለማስቀጠልና ኢትዮጵያን ሥንፈጥር.ዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ

**ትችት!** አበበም እንደልማዱ ሲሽከረከር ቆይቶ ሥሙን ቄስ ይጥራውና የፕሮፌሰርን ሥም በማንሳት የማያውቀውን ከዘላበደ በኋላ በመደምደሚያው "ኢትዮጵያን ሥንፈጥር..." ብሎን አረፈው። ከእነሌንጮ ጋር ነው የሚፈጥሯት፣ ጉድ እኮ ነው፣ጆሮ አልሰማም አይልም፣ ግን በእነአበበ ግንቦት ላይ ዱሮም ዕምነት ሥለማይኖረኝ፣ ምንም አሉ ምን ዋጋ ቢስ ነው። ፕሮፌሰር አሥራትን በተመለከተ ግን "ማን ይናገር የነበረ፣ማን ያርዳ የቀበረ" እንደሚባለው፣ እኔ እሥከማውቀው ድረስ አማራው እነክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ባቋቋሙት በመዐሕድ ድርጅት ውስጥ ተደራጅቶና ታቅፎ ነበር። "በአማራነት ወርጄ አልደራጅም ብሎ ነበር" የሚለው የአበበ ንግግር ከዕውነት የራቀ፣ ከተለመደው ከውሸት ማሕደር የተመዘዘ የበሬ ወለደ ንግግር ነው።

አማራ በፕሮፌሰር ጊዜም ተደራጅቶ ነበር፣ እሳቸው ሲታሰሩና ሲያልፉ፣ አብሮ ታስሮ አለፈ። አሁን ደግሞ አማራ በአዲስ መልክ ተነስቶ እየተደራጀ ነው ምክንያቱም ህልውናው አደጋ ላይ በመውደቁ። ሥለዚህ ከግንቦት ሰባት ጋር የቆመ አማራ በጣት የሚቆጠር እንደሆነ ይታወቃል። በአማራነቱ የሚያምነው በአማራነት ተሰባስቦ እየተዋደቀ ይገኛል። የተወሰኑትን ቀደም ሲል ግንቦት ሰባቶች አባራችኋል። ዛሬ ግን ብዙ አማራ ከእናንተ ጋር እንዳለ ታሥመስላላችሁ እንጅ፣ እህት ርስቴ እንዳጋለጠችው የሥልጣን ጥመኛው ሞላ ይግዛው ዓይነቶቹ በጣት የሚቆጠሩ ብቻ ናቸው።

ሌላው ከግንቦት ሰባቶች ጋር የቀረው ከጉራጌውና ከምባታው በተጨማሪ አማራ ሳይሆን አማርኛ ተናጋሪው፣ግራ የገባው ቅይጡ ብቻ ነው።ይህ ቡድን ወደደም ጠላም አማርኛ ተናጋሪ ነው።አለበለዚያ እርስ በራሱም ሌላ የመግባቢያ ቋንቋ የለውም። ኢትዮጵያን የሚመዘብሯት ትግሬዎችም እኮ አማርኛ እየተናገሩ ነው፣ በአማራው መካከል ተሰግስገው ያጠቁን። ሥለዚህ ግንቦት 7ም ብዙ አማራ አለ እያለ በማታለል አያዘናጋን እንላለን።

ብዙው አማራ በአማራነት ቆሟል፣ ጥቂቶቹ ከወያኔና ከእናንተ ጋር አሉ። እነ ሞላንም ያቀረባችኋቸው ጎንደር አካባቢ አንዳንድ ሰዎችን ሊያሥተዋውቋችሁ እንዲችሉና እየተዋጋን ነው ብላችሁ ለመዋሸት እንድትችሉ እንጅ በዕውቀታቸውና በችሎታቸው እንዳልሆነ የምናውቀው ሀቅ ነው። የጊዜ ጥያቄ ካልሆነ በስተቀር እነኚህን ሠዎችም ነገ ከነገ ወዲያ እንደሸንኮር አገዳ መጣችሁ እንደምትተፏቸው በእርግጠኝነት እናገራለሁ።

አበበ  በግንቦት ሰባት ሽፋን ቢንቀሳቀስም፣ ዘሩ ኦሮሞ  እንደሆነና ዘሩን አቅፎ እየተጓዘ፣ ከእነሌንጮ የኦሮሞ ዘር ድርጅት፣ ከአፋር የዘር ድርጅት እና ከሲዳማ የዘር ድርጅት ጋር “መልከ ጥፉ በሥም ይደግፉ” የሆነ ”ሀገራዊ ንቅናቄ” ተብዬው አቋቁሞ እየሰራ፣ አማራ በአማራነት ትግሉን እንዳይቀጥል “ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት” እንደሚባለው “አማራ በአማራነት ወርጂ አልደራጅም ወያኔ ባሰፋልኝ ሥልቻ አልገባም አለ” እያሉ  ማናፋት  ምኞት ብቻ ከመሆን አያልፍም።

(26) **ጠያቂው** *ሥለ ሀገራዊ ንቅናቄ ተብዬው ይጠይቀዋል።*

**አበበ!** የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ የብሔር ሥብሰቦች  አይደለም፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው። እኛ አርበኞች ግንቦት ሰባት ቅድም እደነገርኩህ የብሔር ድርጅት አይደለንም። የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ኦሮሞዎች ያቋቋሙት ድርጅት ነው። የአፋርን ብትመለከት ወያኔ ሕዝባቸውን በዘር ሥለከፋፈለ በዚህ ሥም ማሰባሰብ ይቀለናል ብለው እንጅ አፋርን እንወክላለን ብለው አይደለም የመጡት፤የሲዳማም እንዲሁ። የፖለቲካ ፕሮግራማቸውንና ዕምነታቸውን በየስብሰባው የሚሉትን ብትሰማ ኢትዮጵያን እንደአገር ለማስቀጠል ነው። ሥለዚህ ይህን ንቅናቄ የብሔረሰቦች ሥብስብ አድርጎ ማዬት ስህተት ነው።

<u>**ትችት**</u>**!** ብርሀኑም ሆነ አበበ እንዲሁም መሰሎቻቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ግራ ከሚያጋቡባቸው አንዱ፣አራት ድርጅቶች የግንቦት 7 ፣የኦሮሞ አዴግ፣ የአፋርና የሲዳሞ፣ ሀገራዊ ንቅናቄ ፈጠሩ የሚሉት ነው። እንዲህ ዓይነቱ እርስ በርሱ የተምታታ ነገር ሕዝቡን ግራ ሥለሚያጋባው ሕዝብም ግራ ሲገባው፣ እሥከሚገባው ጠይቆ ከመረዳት ይልቅ ተስፋ ቆርጦ፣ ማሠብ ያቆማል፣ ወይ በጭፍን ይከተላል፣ወይም ቤቱን ዘግቶ እንዲቀመጥ ይገደዳል።

በቅድሚያ ግልፅ መደረግ የሚገባው በሥም አጠራሮች ሕዝብን ግራ ማጋባትና ማምታታት እንዳይኖር  ማድረግ ነው። የፖለቲካ፣ የብሔር፣ የስፖርት፣ የእርዳታ፣ የስብዓዊ መብት ወዘተ <u>የሁሉም የጋራ መጠሪያ ድርጅት ነው።</u> የኦሮሞ፣የአፋርና የሲዳማ የሚል የታርጋ ሥም ይዘው እሥከወጡ ድረስ  የብሔር ድርጅቶች ናቸው።የብሔር ድርጅቶች ደግሞ የብሔራቸውን ፖለቲካ ያራምዳሉ። ሥለዚህ “መልከ ጥፉ በሥም ይደግፉ ሀገራዊ ንቅናቄ “ተብዬውም የራሱን ብሔር ፍላጎት ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰራ እንጅ ለኢትዮጵያ አንድነት እንደሚሰራ እየተደረገ የሚቀርበው በማር የተጠቀለለ መርዝ ተቀባይነት አይኖረውም።

አበበ ለአለፈው 26 ዓመት የብሔር ፖለቲካ እንደመስፈርት ሆኖ ቆይቷል፣ አሁን ግን ሀገራዊ  ተሳትፎው የበለጠ ነው ምክንያቱም ከኦሮሞ ኮሚኒቲ እንዲሁም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጭምር ተሳትፈዋል። ይህ የማወናበጃ መንገድ በማር የተጠቀለለ መርዝ ነው። ይህ ሊሠመርበት ይገባል። ወያኔ ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያምሰው የኢትዮጵያ አንድነት እንዲመሥል <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ</u> <u>አ</u>ብዮታዊ <u>ዴ</u>ሞክራሲያዊ ግንባር (<u>ኢሕአዴግ</u>) በሚል በማር የተጠቀለለ መርዝ ይዞ ገብቶ እንደሆን መታወቅ ይኖርበታል። ሞኝን ሁለት ጊዜ እባብ ነከሰው እንዳይሆን እንጠንቀቅ።

# ክፍል 5

# አማራ ሆይ!

በቅድሚያ መታወቅ ያለበት  ነገር ቢኖር  ሻዕቢያ ብርሀኑን  የሚፈልገው (1ኛ) ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ (2ኛ) ሻዕቢያን ጠንቅቀው ሳይረዱ ወደ ኤርትራ የሄዱትን ጠንካራ አማራዎች ከእነኮሎኔል ፍፁም ጋር ተሻርኮ ለማስገደልና ለማሳሰር ይጠቅመዋል። እሥካሁንም እንዳደረገው ይነገራል።

ለአማራ ተጋድሎዎች በአገር ውስጥ! በተደጋጋሚ ከብርሀኑ ጎን በቪዲዮ የምናዬው ኤርትራ ውስጥ የሚገኘው የትግሬው ጦር ነው የግንቦት ሰባት መስሏችሁ እንዳትዘናጉ።

ከራሳቸው ከዋኖቹ አንደበት እንደሰማነው የትግሬው ጦር የተቋቋመበት ዋናው ምክንያት አማራው በወያኔ ሥለተሰቃዬ፣ ወያኔ ነገ ቢወድቅ አማራው ትግሬዎችን መበቀሉ ሥለማይቀር ያንን ለመመከት ነው እንጅ ወያኔን ሊወጉ አለመሆኑን ይነግሩናል። ዕውነታው ይህ ነው። ሞኝነት ይብቃ እንንቃ።

አማራው አሁን በመጠናከር ላይ ሥለሆነ፣ በቅድሚያ በብርሀኑ ግንቦት ሰባት ሥምና ምክንያት አብሮ ለመዋጋት በሚል ሰበብ ኤርትራ ውሥጥ ያለው የትግሬ ሕዝብ ዴሞክራቲክ ንቅናቄ-TPDM የትግሬው ጦር ጎንደር ቢገባ የሚወጋው ወያኔን ሳይሆን፣ ዛሬ ወያኔ ጋር ግብግብ የገጠመውን አማራ እንደሆነ ቀድማችሁ ታውቁታላችሁ።

አማራው በጠነከረ ቁጥር ራሱ ሻዕቢያም በጀርባችን ከበሥተኋላ እንደሚወጋን አንጠራጠር። ፀጉረ ልውጥም ሲመጣ በተለይ ደግሞ ትግሬ ከሆነ በመጣበት እግሩ እንዲመለስ አለበለዚያ በሚገባው ቋንቋ እንደምታሥተናግዱትም አልጠራጠርም። እነ ብርሀኑም ገንዘብ ይዘው ሊያዘናጉ ይቀርቧችኋል፣ ግን እንደምታውቁባቸው አልጠራጠርም። አማራው ይህንን ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ አሥገብቶ ነው የሚታገለው ብዬ አሥባለሁ።

<u>**በውጭ አገር የምንገኘውን አማራዎች በተመለከተ!**</u> የትግሬዎቹም የእነ ሌንጮም፣ የደቡቦቹ የእነብርሀኑም አሠራርና አካሄድ አንድ ነው። ይኸውም "አማራ ተቀራርቦ የአማራ አንድነት እንዳይፈጥር፣ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዳይተማመን በማድረግ፣ "እኛ እየተገለገልንበት እንደራጅ፣ አላገለግልም ካለ ደግሞ ከቻልን በመሳሪያ፣ ካልቻልን በፕሮፓጋንዳ መምታትና ግባችንን ማሳካት ነው" ብለው ሲገሰግሱ ይሥተዋላሉ። አማራም ይሁን፣ ትግሬ፣ ጉራጌም ይሁን ከምባታ፣ ሀዲያም ይሁን ኦሮሞ "የኢትዮጵያ አንድነት" የሚለውን ዓረፍተ ነገር ይዞ ብቅ ካለ እኛ አማሮች ዕውነት መሥሎን እንከተላለን ግን መጨረሻው የእኛ መጥፊያ መሆኑን ዘግይተን ነው የምንረዳው። በኢትዮጵያ አንድነት ሥም ለሥልጣንና ለሥውር አጀንዳ እንደሚጠቀሙብን ለመረዳት ፈጣኖች እንሁን። ዳተኝነት ይብቃ።

በአሁኑ ጊዜ አማራነታችን የሚለካው ለአማራው በመቆምና በመታገል እንጅ ከአማራ ሥለተወለደን ብቻ አለመሆኑን እንገንዘብ። ከአማራ ተወልዶ፣ የነገዱ ህልውና አፋፍ ላይ ሲደርስ ለዚያ ያልጮኸ አማራ፣አማራ ነኝ ብሎ የሚያወራበት አንደበት እንዴት ሊኖረው ይችላል።

ዛሬ አማራውን ትጥቅ ለማሥፈታት አፋዊ አንድነቶች ሥለአንድነት ለአማራው ሊነግሩት ይዳዳቸዋል። ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ሠሚ ጆሮም የለንም።

ሥለ አንድነት ለአማራው መንገር ለቀባሪ አረዱት ነው። አማራ 25 ዓመት ሙሉ ያላንዳች ኢጋር ብቻውን ለኢትዮጵያ አንድነት እየጮኸ በገደል ሲወረወር፣ ሲታረድ፣ ሲፈናቀል፣ የአንተ አገር አይደለም ውጣ እየተባለ በአበበ ዘር በኦነግ እና በጃራ

እሥላማዊ የኦሮሞ ድርጅት በሐረር፣ በአሩሲ፣ በወሊጋ ወዘተ እንዲሁም በእነ ብርሀኑም ሆነ በእነ ኤፍሬም ማዴበም ዘሮች ግፍ ሲፈፀምበት ድምፃችሁን አሰምታችሁ አታውቁም። በዘረኞቹ ትግሬዎች የሕዝብ ቆጠራ መሠረት 2.4 ሚሊዮን አማራ መጥፋቱን ገሀድ ማድረጋቸውን ሠምታችኋል።

እኛ ደግሞ 5 ሚሊዮን አማራ መጥፋቱን አረጋግጠናል። ይህ ሁሉ ግፍ ሲደርስ ለ25 ዓመት ያለማቋረጥ፣ አማራ ብለው ሥሙን ጠርተውና ለይተው ሲያጠቁት አንድም ጊዜ "በአማራው ላይ የተደረገውንና የሚደረገውን እናወግዛለን" ብላችሁ አታውቁም። ለኦሮሞው፣ ለአፋሩ፣ ለሲዳማው ወዘተ እያረበዱና ጥብቅና እየቆሙ፣ ዛሬ አማራው ተጎዳሁ፣ የደረሰብኝን የጉዳቴን መጠን የማውቀው እኔው ራሴ ሥለሆንኩ፣ ለራሴ ህልውና እኔው ራሴ እታገላለሁ ብሎ ሲወድቅ ሲነሳ፣ ጉራጌው ብርሀኑ ከምባታው ኤፍሬም ማዲቦና መሰሎቻቸው እኛ እናውቅልሀለን የሚል ድፍረታቸው ምን ያህል አማራውን ቢንቁት ነው፣ ለሰሚውስ አይገርምም?

አማራውን የምትፈልጉት ለአጃቢነት፣ ለገንዘብ እና ለሥልጣን መረማመጃ ብቻ ነው። ሌላው "ሆድ ሲያውቅ፣ ዶሮ ማታ" የሆነው ደግሞ እነ ሌንጮ አንቀፅ 39ንና ክልል ተብዬውን እንደተቀበሉትና እናንተም እነሱን አባብላችሁ አብረዋችሁ እንዲሆኑ ያደረጋችሁት ከወያኔ ጋር ተደራድራችሁ ሥትገቡ ሁላችሁም በድጋሜ አማራውን አግላችሁ ለመርገጥ ነው።

አንድነት፣ የዲሞክራሲ ሥራአት ጅኒጃንካ እያላችሁ አሁን የምትባዝኑትና ቅብጥርጥሩ የበዛው በግርግር አማራውን በማዘናጋት፣ ሻጥር ለመሥራት እንደሆነ ተነቃቅተናል። አማራው አሁን በመኖርና ባለመኖር መካከል ሥለሆነ፣ እያደረገ ያለው ለህልውናው የአርበኝነት ትግል ነው። አሁን በጀመረው መንገድ ቆርጦ መቀጠልና ህልውናውን ማሥጠበቅ ይቀድምበታል።

የእናንተ ዲሞክራሲ አማራውን ለዳግመኛ ጥፋት የሚዳርግ ሥለሆነ አንቀበለውም።

ጆርጅ ቡሽ! ኢራክን ፈረካክሶ የአሜሪካንን ዲሞክራሲ ኢምፖርት (import) ሲያደርግ ሁለት(2) ሃይማኖቶችን ብዙሀኑን ሺያንና አናሳውን ሱኒን (የሳዳም ሁሴንና መሰሎቹ ሀይማኖት) አወዳድሮ፣ ይበልጥ ቁጥር ያለው ሺያ ሥልጣኑን ተረከበ። የተሸነፉትን ሱኒዎች በቁም በቀል አሳደዷቸው። ግድያ፣ እንግልትና መሳደድ ሲበረታ፣ ታሥሮ በወጣው የደህንነት ሰውዬ አሰባሳቢነት ሱኒዎች ትግል ጀመሩ። ትግሉን የጀመሩት ሺያዎችን ለመታገል ቢሆንም ቀስ በቀስ የተለያዩ ፍላጎት ያላቸው ሲሰባሰቡበት መጨረሻው አሸባሪው አይሲስ ሆኖት አረፈ። አንደኛው ሥህተት ዲሞክራሲ ኢምፖርት አይደረግም። ሁለተኛ በሃይማኖት ዲሞክራሲ ምርጫ ትክክለኛ መንገድ አይደለም።

ወደእኛ አገር ወደ ኢትዮጵያ የመጣን እንደሆን ምንጊዜም የዲሞክራሲ ሥርዓት እናስፍን ብንል ሁሉም የዘሩን ወይም የብሔሩን እንደሚመርጥ ሳይታለም የተፈታ ነው። በመሠረቱ በሀይማኖትና በዘር የሚመጣ ሥርዓት አሁን ወያኔ ከሚያራምደው ከዘር ዕልቂት ውጭ አይሆንም።

ይህንን የእነ ግንቦት ሰባት መሪዎች ጠንቅቀው ያውቁታል፣ ግን አሁን እያራመዱ ያለው ለሥልጣን መቆናጠጫ ደጋፊ ላለማጣት ብቻ የሚጠቀሙበት ዜዴ እንደሆነ ያልነቃ ይንቃ። ሥለዚህ ጧት ማታ የሚያደነቁሩበትን ዲሞክራሲ ራሳቸው አጥበው እንዲጠጡት እመክራለሁ።

ልብ ለልብ እሥካልተገናኘንና እካልተማመን ድረስ አሁን ባለው አንዱ ሌላውን አታሎ ወጥመድ ውስጥ አሥገባለሁ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ያውም ደግሞ በከሀዲዎች እንከፍ ፖለቲካ። ዛሬ አማራው ነቅቷል። ዛሬ ከእየአቅጣጫው ፀረ-አማራ ኃይል በተግባር ሌላ፣ በምላስ የኢትዮጵያ አንድነት እያለ እያናፋበት፣ የማንንም መንገደኛና የሥልጣን ጥመኛ አማራው እያጀበ ሥልጣን እያቆናጠጠ፣ ህልውናውን በገዛ እጁ ማጣት በቃኝ ብሏል።

ከአሁን በኋላ ግን በግንቦት ሰባት ሥም የውሸት አንድነት የምትሰብኩን ጉዶች የጉራጌ፣ የከምባታ፣ የኦሮሞና ድብልቆች፣

አማራው እናንተን የሚሸከም ትከሻ የለውምና ከእራሱ ውረዱ እንላለን። አማራው የሚታገለው ወያኔን ብቻ ሳይሆን ከወያኔ ባልተናነሰ መልኩ ፀረ-አማራ የሆኑትንና አገር ሻጮችንም እንደሆነ ቁርጡ ይታወቅልን። አማራው ዛሬ ወያኔን ጥሎ ነገ ሌላ ወያኔ ሥልጣን አያቆናጥጥም።

ከዚህ በተረፈ ከዛሬ ጀምሮ በግልፅ መነገር ያለበት ነገር ቢኖር ግንቦት ሰባት ውስጥ ብዙ አማራ ሳይሆን ያለው ብዙ እንደአማራ አማርኛ ተናጋሪ ደቡቦችና ቅይጦች እንደሆኑ መታወቅ አለበት። አማራማ "አፍንጫ ሲመታ ዓይን ያለቅሳል" እንደሚባለው በአማራነቱ ተሰባስቦ ለገዛ ወንድምና እህቱ ህልውና ቆሞ በመታገል ላይ ነው።

**ከአማራው ጋር ሥምምነት ፈጥሮ መኖር ከተፈለገ**

(1) በመጀመሪያ አማራውን ለትግል ያነሳሳውንና ጫካ ያሥገባውን ምክንያት አውቆ ትግሉን መቀበል የግድ ይላል።

(2) ከዚሁ ጋር የካዳችሁትን የወልቃይት ጥያቄ፣ ሕዝብን ያታለላችሁ መስሏችሁ "ከዲሞክራሲ በኋላ በሕዝበ ውሳኔ" እያላችሁ ማደነጋገሩን ትታችሁ፣ ያላንዳች ማወላወል ዛሬውኑ የአማራ እንጅ የትግሬ እንዳልሆነ አምናችሁ መቀበል፣

(3) ከነፍሰ ገዳዮቹ ከእነ ሌንጮ እርቀት ማሳዬት ምክንያቱም የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በዘር ማጥፋት ወንጀል መጠየቃቸው ሥለማይቀር፣

4) የኢትዮጵያን አንድነት ከዘር ድርጅቶች የፀዳ፣ እንደቅንጅት ለኢትዮጵያ አንድነት በተቋቋሙ ሕብረ ብሔር ድርጅቶች ብቻ ለማምጣት መጣር

(5) አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሠንደቃላማችንን ያላንዳች ማወላወል መቀበል አለባችሁ።

(6) አሁን በአማራው ላይ የምታደርጉትን አሥወግዳችሁ የጎሳዎችን እኩልነት መቀበል፣ወዘተ

(7) ከሻዕቢያ መራቅ፣

ከዚህ ውጭ የሚደረደር የዲሞክራሲ ሥራዓት፣ ወያኔን በጋራ የእንጣል ብልጣብልጥነት፣ ለአማራው በአፍንጫው ይውጣ እንላለን።

"**አማራው!** የኢትዮጵያ አንድነት ብለን ከጠራንለት ከእኛ ጋር ይቆማል" የሚለው አነጋገር ጊዜው ያለፈበት ያረጀ ያፈጀ ፣ ጠላቶቻችን በደካማ ጎናችን እኛን ለእርድ የዳረጉበት አሠራር ነው። ቀጣይነት የለውም።

መሟላት የሚገባቸውን ጉዳዮች እሥካሟላ ድረስ ቢያንስ አንድ ወር ተኩል ቢበዛ ሁለት ወር ከግንቦት ሰባት ጋር ሥለምቆይ፣ሥሜን ከመፃፍ እቆጠባለሁ። እሥከዚያው ሆዳቸውን ይቁረጣቸው።

**የአማራው ሕዝብ በትግሉ ህልውናውን ያሥከብራል!!!**
**በላይ ደጀኔ**